የኢትዮጵያ
ቡናና ሻይ ባለስልጣን
ETHIOPIAN
COFFEE AND TEA AUTHORITY

# የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን
# የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ

ነሐሴ 2013 ዓ/ም
አዲስ አበባ

## ማውጫ


1. መግቢያ .......... 4
2. የባለስልጣኑ፣ተልዕኮ፣ራዕይና እሴቶች .......... 5
3. የበጀት ዓመቱ ዕቅድ መሰረታዊ አቅጣጫ .......... 6
   3.1. ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ .......... 6
   3.2. የግብይት ስርዓቱን ተወዳዳሪነት ማሳደግ .......... 6
   3.3. በዘርፉ ለስራ ዕድል ፈጠራ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር .......... 6
4. የዕቅድ ዝግጅት ሂደቶች .......... 7
5. የዕቅዱ መነሻዎች .......... 7
   5.1. የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት .......... 7
   5.2. የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ .......... 8
   5.3. የ2013 ምርት ዘመን ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ እንደ መነሻ .......... 8
6. የ2013 ምርት ዘመን ዕቅድ አፈጻጸም .......... 9
   6.1. የልማት ዘርፍ ዕቅድ አፈጻጸም .......... 9
      6.1.1. ምርትና ምርታማነት ማሳደግ .......... 9
      6.1.2. የዘር ብዜት፣ የግብዓት አቅርቦትና ጥራት ቁጥጥር .......... 10
      6.1.3. የቡና ምርት ዝግጅት .......... 11
   6.2. የግብይት ዘርፍ ተግባራት አፈጻጸም .......... 13
      6.2.1. የወጪ ንግድ ዕቅድ አፈጻጸም .......... 13
      6.2.2. የወጪ ንግድ በመጠንና በገቢ ለማሳደግ የተከናወኑ ተግባራት .......... 14
7. የ2014 ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች .......... 20
   7.1. ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ .......... 20
   7.2. የወጪ ንግድን በመጠንና በገቢ ማሳደግ .......... 21
   7.3. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች .......... 22
8. የዕቅዱ ማስፈፀሚያ ስልቶች .......... 23
   8.1. ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚከናወኑ ተግባራት .......... 23
      8.1.1. የኤክስቴንሽን ተደራሽነት ማስፋፋት .......... 23

8.1.2. የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ማሳ እንክብካቤ ስራዎች ..... 23
8.1.3. በሽታና ተባይ መከላከልና መቆጣጠር ..... 24
8.1.4. የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ማሳ ሽፋን ማሳደግ ..... 26
8.1.5. የተሻሻለ የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ግብዓት አቅርቦት ማሳደግ ..... 28
8.1.6. የግብዓት አቅርቦት ..... 29
8.1.7. ድህረ ምርት ዝግጅት እና ጥራት አጠባበቅ አሴት ጭመራ ..... 30
8.1.8. የልማት አካላት ግንኙነት ማጠናከር ..... 33
8.1.9. የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር አሠራርን ማዘመንና ማጠናከር ..... 34
8.1.10. የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም መገንባታ ..... 34
8.2. የወጪ ንግድ መጠንና ገቢ ለማሳደግ የሚከናወኑ ተግባራት ..... 35
8.2.1. የምርት አቅርቦትን ማሳደግ ..... 35
8.2.2. የቀረበውን ምርት ወደ ውጭ ገበያ እንዲላክ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ..... 36
8.2.3. የመረጃ ትንተና በማድረግ የመረጃ አቅርቦት እና የገበያ ድርሻን ማሳደግ፣ ..... 36
8.2.4. የምርት ጥራት ምርመራ አገልግሎት መስጠት ..... 37
8.2.5. ቅንጅታዊ አሰራርን ማሳደግ፣ ..... 38
8.2.6. የአሠራር ስርዓቶችን ማሻሻል ..... 38
8.3. የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር አሠራርን ማዘመንና ማጠናከር ..... 39
9. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች ..... 39
10. ማጠቃለያ ..... 40
11. አባሪ ..... 41
1. በ2014 የምርት ዘመን የቡና ሻይና ቅ/ቅመም ምርትና ምርታማነት እቅድ ..... 41
2. በ2014 በጀት ዓመት የቡና ኤክስፖርት የመጠንና ገቢ ዕቅድ ..... 46
3. በ2014 በጀት ዓመት የቅ/ቅመም ኤክስፖርት የመጠንና ገቢ ዕቅድ ..... 47
4. በ2014 በጀት ዓመት የሻይ ኤክስፖርት የመጠንና ገቢ ዕቅድ ..... 48

## 1. መግቢያ

መንግስት በቀጣይ አስር ዓመታት 10% አማካይ ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ የዜጎችን የነፍስ ወከፍ ገቢ በሶስት እጥፍ ለማሳደግ፣ ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ዜጎችን ብዛት ከ19% ወደ 7% ዝቅ በማድረግ ሀገራዊና የዜጎችን ብልጽግና ለማረጋገጥ እንደሚሠራ ይፋ አድርጓል፡፡ ከዚህም በመነሳት በቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማትና ግብይት ዘርፍ የተሳተፉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተመጋገበና የተቀናጀ ርብርብ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ባለስልጣኑ የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርትና ማርታማነት በማሳደግ፣ ጥራትን በማሻሻልና ፍትሃዊ፣ ዘመናዊና ተወዳዳሪ የግብይት ሥርዓት በመገንባት ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ግኝት የማሳደግና በዘርፉ የተሰማሩና የሚሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ገቢ በማሳደግ ኑሯቸውን በመሰረታዊነት ለመለወጥ የሚያስችሉ ተግባርና ኃላፊነትን ይዞ የሚንቀሳቀስ ሲሆን ይህንንም ተግባርና ኃላፊነት ለማሳከት የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የልማትና የግብይት ዕቅድ አዘጋጅቶ ለተግባራዊነቱ እየተጋ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት በተደረጉ የአሠራር፣ የአደረጃጀትና የአመራር ለውጦች እና ሪፎርሞች ምርትና ምርታማነት፣ ጥራትና የወጪ ንግድ መጠን መሻሻል እያሳየ ይገኛል፡፡ በቀጣይም ሀገራዊ የዕድገት ግቦች መሠረታዊ የአስተሳሰብና የተግባር ለውጥ የሚፈልጉ በመሆናቸው ዘርፉ በአሁኑ ወቅት ያለበትን ሁኔታ በመዳሰስ ተሞክሮ በመቀመርና አዳዲስ የአፈጻጸም አቅጣጫዎች በመቀየስ በትኩረት ወደ ተግባር የሚገባ ይሆናል፡፡

በዚህ መሠረት የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ጥራትን ለማሻሻልና የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማሳደግ የሚያስችሉ የኤክስትንሽን፣ የግብዓት አቅርቦት፣ የሰብል ጥበቃ፣ ድህረ ምርት አያያዝና አግሮፕሮሴሲንግ እና ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት በመገንባት በሀገራችን ቀጣይነት ያለው ዕድገት ተጠቃሚነት

ለማረጋገጥ እንዲቻል ባለስልጣኑ በ2014 በጀት ዓመት ለመፈጸም ያዘጋጀው ዓመታዊ ዕቅድ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2. የባለስልጣኑ፣ተልዕኮ፣ራዕይና እሴቶች

**ተልዕኮ**

በቡና፣ ሻይና ቅመማቅመም ሰብሎች ልማት፣ አግሮ ፕሮሰሲንግና ግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ተግዳሮቶች በመለየት፣ የመፍትሄ ስልቶችን በመንደፍና በመተግበር፣ የምርምርና ጥናት ግኝቶችን በማስረፅ፣ የተሻሻሉና ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችንና ግብአቶችን በመጠቀም፣ ተገልጋይ ተኮር የኤክስቴንሽን ሥርዓትን ተደራሽነት በማሳደግ፣ ልዩ ልዩ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን በመስጠት፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋት በከፍተኛ መጠን ምርትና ምርታማነትን በቀጣይነት ማሳደግና ዕሴት በመጨመር ለሀገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ ብሎም በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ መሆን፣ ዘመናዊ የመረጃ፣ የግብይትና የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ከዘርፉ ለኢኮኖሚው ዕድገት የሚፈለገውን የውጭ ምንዛሪ ግኝትን የማሳደግ፣ የአምራቹንና የግብይት ተዋንያኑን ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ማረጋገጥ ነው፡፡

**ራዕይ**

በ2017 በዘመናዊ የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማትና ግብይት ያደገ ኢኮኖሚና ከድህነት የተላቀቀ ህብረተሰብ ተፈጥሮ ማየት፣

**ዕሴቶች**

- የተገልጋይ እርካታና ተጠቃሚነት፣
- የስራና የለውጥ ባህል ማዳበር፣
- ሙስናን መጸየፍ፣
- የመልካም አስተዳደር ማስፈን፣
- ተቋማዊና ሙያዊ አጋርነት፣
- የሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት፤
- ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ልማት፣

# 3. የበጀት ዓመቱ ዕቅድ መሰረታዊ አቅጣጫ

## 3.1. ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ

የተሻሻሉ የግብርና አሰራር ዘዴዎችን መጠቀም የሚያስችል ዘመናዊ የኤክስቴንሽን ስርዓት በመዘርጋትና ተደራሽ በማድረግ፣ ምርጥ ተሞክሮ በመቀመርና በማስፋት የአምራቹን ዕውቀትና ክህሎትን የማሻሻል፣ የግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም የማሳደግ፣ የድህረ-ምርት አያያዝና ጥራት የማሻሻል፣ የምርቶችን አግሮ-ፕሮሴሲንግን የማስፋፋት እና በዘርፉ የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን የማሳደግ፣ አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች እና በሰፋፊ እርሻዎች ልማት የሚገኝ የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርትና ምርታማነት የማሳደግ ሥራ ይሰራል፡፡

## 3.2. የግብይት ስርዓቱን ተወዳዳሪነት ማሳደግ

የአምራቹን፣ የግብይት ተዋንያንን እንዲሁም ሀገራዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ግብይት ሰንሰለት ላይ የሚስተዋሉ ማነቆዎችን የመፍታት፣ ዘመናዊ የገበያ መረጃ ስርዓት የመዘርጋትና የማስፋፋት፣ የጥራት ምርመራና እና የሰርተፊኬሽን አገልግሎትን የማዘመን፣ የክምችትና የኮንትራት አስተዳደርን የማሳለጥ፣ በጥሬና እሴት በተጨመረ የምርት ብራንዲንግ እና የገበያ ፕሮሞሽን ተግባራትን በመፈጸም በነባርና አዳዲስ መዳረሻ ገበያዎች ድርሻችንን የማሳደግ፣ የላኪዎቻችንን ምርት ግዢ፣ ዝግጅት፣ ሽያጭ እና የመላክ ዕውቀትና ክህሎት እንዲሁም የፋይናንስ አቅም የማሳደግ ሥራ በትኩረት ይሰራል፡፡

## 3.3. በዘርፉ ለስራ ዕድል ፈጠራ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር

የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ንዑስ ዘርፍ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሃገራችንን 25 በመቶ ህዝብ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ በተለይ የሴቶችና ወጣቶች የሥራ አጥነት ችግር በመቅረፍ ረገድ ከችግኝ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ወጪ ንግድ ባሉ ደረጃዎች ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠር ይቻላል፡፡ ስለሆነም የወጣቶችና ሴትች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ስልቶችን በመንደፍና ሁኔታዎችን በማመቻቸት

በችግኝ ዝግጅትና ስርጭት፣ በግብዓት አቅርቦትና ስርጭት፣ በመካከለኛና ሰፋፊ እርሻዎች ምርት በመሰብሰብ፣ በአቅርቦትና በኤክስፖርት ምርት ዝግጅት እና በመሳሰሉት መስኮች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር በትኩረት ይሠራል፡፡

## 4. የዕቅድ ዝግጅት ሂደቶች

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ የግብርና ዘርፍ የቀጣይ አስር ዓመታት መሪ ዕቅድ መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን ንዑስ ዘርፉ ለሀገራዊ ዕድገት ማበርከት ያለበትን አስተዋፅኦ እና በቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማትና ግብይት የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በመሪ ዕቅዱ በሁለተኛው ዓመት የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት እንዲያስችል ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ በዝግጅቱም የሚመለከታቸው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተሳተፉ ሲሆን ትግበራው የክልሎችን፣ የግብይት ተዋንያንን እና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ እነዚህ አካላት እንዲሳተፉ እና እንዲያዳብሩት ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ ጥራትን የሚያሻሽሉ፣ ምርታማነትን እና የወጪ ንግድን ሊያሳድጉ የሚችሉ ዝርዝር ተግባራት በግልጽ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ ለዕቅድ ዝግጅቱ ጥቅም ላይ የዋሉ አሃዛዊ መረጃዎች ከማዕከላዊ ስታቲስትክስ ኤጀንስ፣ ከባለስልጣኑ የክትትል መረጃ፣ ከጉምሩክ ባለስልጣን እና ከብሔራዊ ባንክ የተገኙ ናቸው፡፡

## 5. የዕቅዱ መነሻዎች

### 5.1. የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት

ባለስልጣኑ በቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ሰብሎች ልማት እና አግሮ ፕሮሴሲንግ እሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ተግዳሮቶች በመለየት፣ የመፍትሄ ስልቶችን በመንደፍና በመተግበር፣ የምርምርና ጥናት ግኝቶችን በማስረፅ፣ የተሻሻሉና ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችንና ግብአቶችን በማቅረብና በመጠቀም፣ ተገቢ ትኩረት ያልተሰጠው የኤክስቴንሽን ሥርዓትና ተደራሽነት በማሳደግ፣ ልዩ ልዩ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን በመስጠት፣

ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋት በከፍተኛ መጠን ምርትና ምርታማነትን በቀጣይነት ማሳደግና ዕሴት በመጨመር ከዘርፉ ለኢኮኖሚው ዕድገት የሚፈለገውን የውጭ ምንዛሪ ግኝትን የማሳደግ፣ የአምራቹን  ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ለማረጋገጥ የተቋቋመ እንደመሆኑ ይህን ተልዕኮ ለማሳካት የተሰጠው ኃላፊነት ለዕቅዱ መነሻ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

## 5.2. የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ

በሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና የግብርና ሴክተር አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ ያስገባ የዘርፍ ዕቅድ ማዘጋጀት ተገቢ በመሆኑ በሚቀጥሉት 10 (አስር) ዓመታት የግብርና ዘርፍ አማካይ 6.02 በመቶ እድገት ለማስመዝገብ የሚያስችል የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርትና ምርታማነት እንዲሁም የወጪ ንግድ ዕድገት ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ የሚጠበቅ ውጤት ታሳቢ ተደርጓል፡፡

## 5.3. የ2013 ምርት ዘመን ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ እንደ መነሻ

በ2013 ምርት ዘመን ዕቅድ ዝግጅት እና አፈጻጸም ወቀት የተገኙ መልካም ልምዶችን በቀጣይ አስፍቶ ለማስኬድ እና በድክመት የተለዩ ጉዳዮችን ማስተካከል እንደሚገባ በመገንዘብ ለ2014 ምርት ዘመን ዕቅድ ዝግጅት መነሻ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

# 6. የ2013 ምርት ዘመን ዕቅድ አፈጻጸም

## 6.1. የልማት ዘርፍ ዕቅድ አፈጻጸም

### 6.1.1. ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

ቡና

በ2012/13 ምርት ዘመን የቡና ማሣ ምርታማነት ማሻሻያ ሥራዎችን በመፈፀም ለምርት የደረሰውን 861,435 ሄ/ር የቡና ማሣ ምርታማነቱን በሄ/ር 6.38 ኩ/ል ከነበረበት ወደ 7.9 ኩ/ል በማድረስ 683,146 ቶን ምርት ለማምረት ግብ ተይዞ በባለስልጣኑ በተካሄደዉ የቡና ቅድመ-ምርት ትመና ፈጣን ዳሰሳ ጥናት መሰረት ምርት መስጠት ከሚችለው 913,368 ሄ/ር የቡና መሬት ላይ 680,800 ቶን ምርት የተገኘ ሲሆን ምርታማነቱ 7.5 ኩ/ል/ሄ/ር እንደሚሆን ተገምቷል፡፡

የዕቅድ ዘመኑ የምርትና ምርታማነት ግቦች ካለን ተፈጥሯዊ እና መዋቅራዊ አቅም አኳያ ሊደረስበት የሚችል ቢሆንም የተቀመጡ የምርታማነት ማሳደጊያ ተግባራት አፈጻጸም ላይ የነበረው ጉድለት ለአፈጻጸሙ ማነስ ቁልፍ ሚና ተጫውቷል፡፡

ስለሆነም በተሻሻሉ የምርታማነት ማሳደጊያ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ላይ የነበሩ ጉድለቶችን በማረም፣ የኤክስቴንሽን ተደራሽነትና ጥራት በማሳደግ፣ የግብዓት አቅርቦት ሥርዓት በማሻሻል፣ በተለያዩ ምክንያቶች ምርት መስጠት ያቆሙ እና ምርት የቀነሱ ማሳዎችን በማደስ ምርታማነትን በቀጣይነት ለማሳደግ መስራት ይገባል፡፡

ሻይ

በ2012/13 ምርት ዘመን በአልሚ ባለሀብቶች ከ2,760 ሄክታር ላይ 10417 ቶን ምርት በማምረት ምርታማነትን በአማካይ 37.5 ኩ/ል ለማድረስ ታቅዶ 10,304 ቶን ምርት በማምረት ምርታማነትን 37.3 ኩ/ል/ሄ/ር (99.5%) ማድረስ ተችሏል፡፡

እንዲሁም በአውት ግሮወርስ ከ 482 ሄክታር ላይ ምርታማነትን 23 ኩ/ል/ሄር በማድረስ በዓመቱ 1126 ቶን ለማምረት ታቅዶ 1126 ቶን (100%) ደረቅ ሻይ ምርት ተመርቷል፡፡ በዚህ መሰረት ምርታማነትን 23 ኩ/ል/ሄ/ር ማድረስ ተችሏል፡፡ በትስስር እያለሙ የሚገኙ 925 ወንዶችና 70 ሴቶች በድምሩ 995 አ/አደሮች በልማቱ ተሳትፈዋል፡፡

ሻይን በአርሶ አደር ደረጃ አልምቶ ለገበያ ለማቅረብ ቀላል የሆነ ሻይ ማዘጋጃ ቴክኖሎጂ አለመኖር፤ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ወጭ መጠየቁ ፤ለሻይ ልማት የተሰጠዉ ትኩረት በቂ አለመሆን እና በምርምር አለመደገፉ፤ በሻይ ልማት ተሳታፊ አርሶ አደሮች እና በሻይ አልሚ ድርጅቶች እየለማ የሚገኘዉ የሻይ ልማት እንዳይስፋፋ ማድረጉ ተለይትዋል።

### የቅመማ ቅመም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ

በምርት ዘመኑ 364,006 ሄ/ር ማሳ በተለያዩ የቅ/ቅመም ሰብሎች ለመሸፈንና 720 ሺህ ቶን ምርት ለማምረት ታቅዶ 360,289 ሄር (99%) ማሳ በማልማት 644.3 ሺህ ቶን (89%) ተሰብስቧል፡፡ የዋና ዋና ቅመም ምርቶች አፈጻጸም በዝርዝር ሲታይ፡- የዝንጅብል ልማት በማሳ ሽፋንም ሆነ በምርት 100% የተፈጸመ ሲሆን በርበሬ በማሳ ሽፋን 95% በምርት 79%፣ ኮረሪማ በማሳ ሽፋን 100% በምርት 86%፣ ዕርድ በማሳ ሽፋንም ሆነ በምርት 100% አፈጻጸም ተመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ የቅመማቅመም ምርትና ምርታማነትን በቀጣይነት ከማሳደግ አኳያ ያለንበትን ደረጃ ስንፈትሽ በምርጥ ዘር ዕጥረት፤ በበሽታና ተባይ ክስተት መጨመር፤ የተሻለ ቴክኖሎጂ አቅርቦት ችግርና ለአርሶ አደሩም የሚደረገው ድጋፍ አነስተኛ በመሆኑ በመጠንና በጥራት አምርተን ለኤክስፖርቱ የሚመጥን ምርት ከማግኘት አንጻር ብዙ የሚቀረን ስራ እንዳለ የሚያሳየን ሲሆን በምርትና ምርታማነት ዕድገት ላይ የሚፈለገው ውጤት ላይ ስላልተደረሰ በቀጣይ እነዚህን ተጋዳሮቶች ለይቶ መስራት ተገቢ ይሆናል፡፡

### 6.1.2. የዘር ብዜት፣ የግብዓት አቅርቦትና ጥራት ቁጥጥር

#### ቡና

በበጀት ዓመቱ በቡና ዘር ብዜትና አቅርቦት 5,450 ኩ/ል የቡና ዘር ለማዘጋጀት ታቅዶ 5,609 (103%) ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም ለ2013 ተከላ የሚውል 1.53 ቢሊዮን የቡና ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ ከፈሰሰው 5,529.44 ኩ/ል በቁጥርም 1,757,689,375 ዘር ውስጥ 1,482,939,038 የበቀለ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 1,376,371,655 ችግኞች በሕይወት ያሉ በመሆናቸው በእንክብካቤ ላይ ይገኛሉ፡፡

**ቅመማ ቅመም**

በበጀት ዓመቱ ከምርምር ማዕከላት የቅመማ ቅመም ዘሮችን በማሰባሰብ የዋና ዋና ቅመማ ቅመም ሰብሎች የተሻሻሉ ዝርያዎች በተመረጡ የመንግስት ችግኝ ጣቢያዎች በመሞከር ውጤታማነታቸውን ለአርሶ አደር በማስተዋወቅ በቀጣይ ወደ ዘር ብዜት ለማስገባት ከተለያዩ ምርምር ማዕከላት 30.5 ኪ.ግ የተለያዩ የቅ/ቅመም ዝርያዎች ለማሰባሰብ ታቅዶ ከደ/ዘይት፣ መልካሳ፣ ሲናና እና ጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከላት ጥቁር አዝሙድ 9.8 ኪ.ግ፣ ነጭ አዝሙድ፣ 3 ኪ.ግ፣ አብሽ 10 ኪ.ግ፣ ድንብላል 4 ኪ.ግ እና በርበሬ 0.54 ኪ.ግ በድምሩ 27.34 ኪ.ግ (89%) በማሰባሰብ ለክልሎች ማሰራጨት ተችሏል፡፡

**ሻይ**

በበጀት ዓመቱ 4,000,000 የሻይ ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ 3,085,135 (77.13 %) ችግኞች ተዘጋጅተው እንክብካቤ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡

**የቃጫ ጆንያ አቅርቦት**

1502700 ባለ 100 ኪ.ግ ቡና ማቅረቢያ ጆንያ ለማቅረብ ታቅዶ 3,118,000፤ 18665 ባለ 30 ኪ.ግ ቡና ማቅረቢያ ጆንያ ለማቅረብ ታቅዶ 468,000 እንዲሁም 200000ካ.ሜ. ዝርግ ጆንየ ለማቅረብ ታቅዶ 549884 ካ.ሜ በሀገር ውስጥ ጆንያ አምራቾች ተመርቶ ቀርቧል፡፡

የቡና መላኪያ ጆንያ (ባለ 60 ኪ.ግ እና ባለ 50 ኪ.ግ) በቁጥር 2,145,000 ለማቅረብ ታቅዶ 2,974,765 በማቅረብ ከዕቅዱ በላይ ተከናውኗል፡፡

### 6.1.3. የቡና ምርት ዝግጅት

**የታጠበ ቡና ምርት ዝግጅትና ጥራት ማሻሻያ**

የታጠበ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች በግል፣ በአክሲዮንና በህብረት ሥራ ማህበራት ከሚገኙ በቁጥር 1,450 ውስጥ 1,257 (86.7%) ኢንዱስትሪዎች የቅድመ ዝግጅት ስራ በማጠናቀቅ ወደ ስራ የገቡ ሲሆን ቀሪዎቹ 193 ኢንዱስትሪዎች በዓለም ገበያ ላይ የቡና ዋጋ መውረድና ኪሳራን በመስጋት፣ በተወሰኑ አካባቢዎች ባለው ፀጥታ ችግር፣ የገንዘብ ብድር አቅርቦት አለመመቻቸት፣ የመሰረተ-ልማት ያለመሟላት የተነሳ ወደ ሥራ አልገቡም፡፡

በበጀት ዓመቱ 697 ሺ.ህ ቶን ቀይ እሸት ቡና ለመሰብሰብ ታቅዶ 739.9 ሺ.ህ ቶን (100% በላይ)፣ እንዲሁም 129 ሺ.ህ ቶን የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ ለማዘጋጀት ታቅዶ 135.5 ሺ.ህ ቶን (100% በላይ) ተከናውኗል፡፡

### የደረቅ ቡና ምርት ዝግጅትና ጥራት ማሻሻያ ስራዎች

የደረቅ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች በግል፣ በአክሲዮንና በህብረት ሥራ ማህበራት ከሚገኙ በቁጥር 944 ውስጥ 676 (72%) ኢንዱስትሪዎች የቅድመ ዝግጅት ስራ በማጠናቀቅ ወደ ስራ የገቡ ሲሆን ቀሪዎቹ 268 ኢንዱስትሪዎች በተወሰኑ አካባቢዎች ባለው የፀጥታ ችግር፣ የገንዘብ ብድር አቅርቦት ችግር እና በተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች የተነሳ ወደ ሥራ እንዳልገቡ ታውቋል፡፡

### የቅመማ ቅመም ምርት ዝግጅት እና ጥራት ማሻሻያ

ምክረ-ሀሳቡን ተከትሎ የቅመማ ቅመም ምርቶችን በማድረቅ የጥራት ደረጃን ለማሻሻል እንዲቻል በዓመቱ 53 ሺ.ህ ካ.ሜትር በተለያዩ አማራጮች የማድረቂያ አልጋ እንዲሰራ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 60.1 ሺ.ህ ካሬ ሜትር ከዕቅድ አንጻር (100% በላይ) ማከናወን ተችሏል፡፡

የበርበሬ፣ ዝንጅብል፣ ኮረሪማ፣ ዕርድ፣ አብሽና አዝሙድ እና ሌሎች ቅመማ ቅመሞች በበጀት ዓመቱ 661.8 ሺ.ህ ቶን ምርት ለማዘጋጀት ታቅዶ 390.723 ሽህ ቶን 59% ተከናውኗል፡፡

### የሻይ ምርት ዝግጅትን በተመለከተ

በሻይ አልሚ አርሶ አደሮች እና ልማት ድርጅቶች ከሚለማውና ምርት መስጠት ከሚችለው የሻይ ማሳ በበጀት ዓመቱ 11.766 ሺ.ህ ቶን ደረቅ የሻይ ምርት እንደሚዘጋጅ ታቅዶ 11,430 ቶን የሻይ ቅጠል (›100%) ምርት እንደተዘጋጀ ተረጋግጧል፡፡

### ዕሴት የተጨመረባቸው ምርቶች ምርት ዝግጅት

ዕሴት የተጨመረበት የቡናና የቅመማቅመም ምርት ለሃገር ውስጥ እና ለውጪ ገበያ እንደሚቀርብ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 0.99 ሺ.ህ ቶን ተቆልቶ የተዘጋጀ ቡና እና 0.011 ሺ.ህ ቶን የቅመማ ቅመም ምርት ለውጪ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ ተቆልቶ የተዘጋጀ ቡና 0.42 ሺ.ህ ቶን (43%) እና የቅመ ማቅመም ምርት 2.18 ሺ.ህ ቶን (>100%) ማከናወን ተችሏል፡፡

## 6.2. የግብይት ዘርፍ ተግባራት አፈጻጸም

### 6.2.1. የወጪ ንግድ ዕቅድ አፈጻጸም

**ቡና**

በበጀት ዓመቱ 312,061.74 ቶን ቡና በመላክ 1,173.49 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 248,311.66 ቶን (ከዕቅዱ 80%) በመላክ 907.04 ሚሊየን የአሜርካን ዶላር (ከዕቅዱ 77%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን -22,523.47 ቶን (-8.32%) ቅናሽ በገቢ ደግሞ 52.83 ሚሊዬን ዶላር (6.19%) እድገት ተመዝግቧል፡፡

**ቅመማ ቅመም**

በበጀት ዓመቱ 15,000 ቶን ቅመማ ቅመም በመላክ 18.78 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 12,880 ቶን (ከዕቅዱ 86%) በመላክ 15.71 ሚሊየን የአሜርካን ዶላር (ከዕቅዱ 84%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ካለፈው በጀት ዓመት በተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን 983ቶን(8.26%) ጭማሪ እና በገቢ ደግሞ -0.30 ሚሊዬንዶላር(-1.89%) ቅናሽ ተመዝግቧል፡፡

**ሻይ**

በበጀት ዓመቱ 2,104.1 ቶን ሻይ በመላክ 3.53 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 1,814.5ቶን (ከዕቅዱ 86%) በመላክ 2.93 ሚሊየን የአሜርካን ዶላር (ከዕቅዱ 83%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ካለፈው በጀት ዓመት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን 49.80ቶን (2.82%) እና በገቢ ደግሞ 0.28 ሚሊዬን ዶላር (10.64%) ጭማሪ ተመዝግቧል፡፡

**ጠቅላላ የወጪ ንግድ**

በበጀት ዓመቱ 329,165.84 ቶን የቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ምርቶችን በመላክ 1,195.82 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 263,006.16 ቶን (ከዕቅዱ 80%) በመላክ 925.68 ሚሊየን የአሜርካን ዶላር (ከዕቅዱ 77%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ካለፈው በጀት ዓመት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን -21,490.67 ቶን (-7.55%) ቅናሽ እና በገቢ ደግሞ 52.81 ሚሊዬን ዶላር (6.05%) እድገት ተመዝግቧል፡፡

### 6.2.2. የወጪ ንግድ በመጠንና በገቢ ለማሳደግ የተከናወኑ ተግባራት ድጋፍና ክትትል

- 125 ቡናላኪዎች 30 የሻይና ቅመማቅመም ላኪዎችን በቢዝነስ ፕላን እንዲመሩ ለማድረግ ታቅዶ 95 ላኪዎች በቡና 25 በቅመማ ቅመም የወጪ ንግድ የብዚነስ ፕላናቸውን እንዲያዘጋጁ ድጋፍ ተደርጓል፣
- ላኪዎች በወቅቱ ቡና ገዝተው ኤክስፖርት እንዲያደርጉ የአካል እና ተደጋጋሚ የስልክ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡
- በኤክስፖርት ሂደት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች በወቅቱና በሚፈለገው የአገልግሎት የጥራት ደረጃ ለኤክስፖርተሮች እንዲሰጡ ኮሚቴ በማዋቀር ወቅታዊ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ ተደርጓል
- በላኪዎችና አቅራቢዎች በቀጥታ የግብይት ትስስር ከ1ኛ እስከ 4ኛ ደረጃ 750 እንዲሁም 5 እና ከዚያ በታች የጥራት ደረጃ 623 በድምሩ 1373 የግብይት ትስስር ተፈጥሯል፡፡
- ነባርና አዳዲስ የቡና ግብይት ተዋንያን ብቃታቸው እየተረጋገጠ ወደ ግብይቱ እንዲገቡ 887 አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ለኮሜሪሻል ላኪ፣ ለአርሶ አደር ላኪ፣ ለአልሚ ላኪ፣ ለአቅራቢ ላኪ እና 87 ለማዘጋጃ ኢንዱስትሪ የተሰጠ ሲሆን 470 ነባር የግብይት ተዋንያኖች የብቃት ማረጋገጫ እንዲታደስ ተደርጓል፡፡
- በወቅታዊ የኤክስፖት አፈጻፀም ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በበጀት ዓመቱ ሁለት ጊዜ የምክክር መድረኮች እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡
- የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለቡና ኤክስፖርት እንዲውል ሁሉም ላኪ ድርጅቶች አገልግሎቱን እንዲያውቁና እንዲጠቀሙ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን የእንዶዴ ጣቢያ በሳምንት ሁለት ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡
- የቡና ምርት በጥራትና በብዛት ወደ ግብይት ማዕከላት እንዲቀርብ ከማድረግ አንጻር ከክልሎች ጋር በመቀናጀት የከረመ የቡና ምርት ወደ ገበያ እንዲቀርብና እና ለአዲሱ ምርት ግብይት በቂ ዝግጅት እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፤

- አዲስ የተካተቱ የግብይት አሰራሮች ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር 762 ለሚሆኑ የግብይት ተዋንያንና በየደረጃው ለሚገኙ ለወረዳ፣ ለዞንና ለክልል አስፈጻሚ ባለሙያዎችና አመራሮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

- አዳዲስ የምርት ዝግጅት ልምዶችን ተግባራዊ ለማድረግ ለሚፈልጉ ላኪ ድርጅቶች በቂ ድጋፍ እንዲያገኙ ከክልሎች ጋር በመነጋገር ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- አዲስ የወጣው የገንዘብ ዝውውር መመሪያ በቡና ንግድ ላይ ችግር እናዳይፈጥር ከብሄራዊ ባንክ ጋር በመመካከር በልዩ ሁኔታ እንዲስተናገዱ አሰራረር እንዲዘረጋ ተደርጓል፡፡
- አዲስ በተጀመረውና እየተተገበረ ባለው የኦን ላይን እና የአንድ መስኮት አገልግሎት አሰጣጥ ምክንያት የተፈጠረውን የግንዛቤ ክፍተት ከጉምሩክ ጋር በመነጋገር ለመፍታት ጥረት ተደርጓል።

**የገበያ ድርሻን ለማሳግ**

- ❖ ከግብይት ተዋንያን እና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በበይነመረብ/virtual meeting አማካይነት በነባርና አዳዲስ የቡና ዋና ዋና ገበያ መዳረሻዎች ከቤልጅየም ፣ ሉክሰንበርግ ፣ፈረንሳይ፣ ቻይና፣ እንግሊዝ እና እስራኤል ቡናችንን የማስተዋወቅና የገበያ ማስፋፊያ ስራዎች ተደርጓል፡፡
- ❖ በታዳጊ የቡና ገበያ መዳረሻዎች (አውስትራሊያ፣ ሩሲያ፣ ካናዳ እና ቻይና) ጥናትን መሰረት ያደረገ የገበያ ማስፋፊያ ስራዎችን ለማካሄድ ታቅዶ በበይነ-መረብ አማካይነት ከዮሮ- ኤዥያ (ሩሲያ፣ ቤላሩስ፣ አርመንያ) ቡና ገዥዎች ጋር በሩሲያ ሞስኮ በበይነ-መረብ የቀጥታ ውይይት የተደረገ ሲሆን በኹነቱ ላይ 58 ቡና ላኪዎች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡
- ❖ በእስራኤል የሀገራችንን ቡና የሽያጭ አድማስ ለማስፋት ከውጭ ጉዳይ እና ከእስራኤል የኢትዮጵያ ኢምባሲ ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ ቡና ምንነት፣ የሀገራችንን ቡና በእስራኤል ሀገር ማስተዋወቅ በሚቻልበት ሁኔታ ዙሪያ በስፋት ውይይት ተደርጎበት ከሁለቱም ወገን ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡
- ❖ ደቡብ ኮሪያ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ የንግድ ፕሮሞሽን ዌብናር እ.አ.አ ማርች 11 ቀን በሴዑል የንግድ ፕሮሞሽን መድረክ በማዘጋጀት የሀገራችን ቡና ማህበራቶች

ደቡብ ኮሪያ ከሚገኙ ቡና ገዥዎች ጋር በፎረሙ ላይ ገለጻ (በቀጥታ) በማድረግ እንዲገናኙ ተደርጓል፡፡

- ❖ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካይነት ጀርመን ሀገር በርሊን ከሚገኘው ኤምባሲ Hatra GmbH የተባለው የተለያዩ ዓይነትና መጠን ያላቸውን የሀገራችንን ቡና ለመግዛት በተጠያቀው መሰረት የኩባንያው ፍላጎት ሊያሟሉ የሚችሉ በ2013 ዓ.ም በቢዝነስ ፕላን የሚመሩ የሀገራችን ቡና ላኪ ድርጅቶች ዝርዝር አድራሻ የመላክ ሥራ ተከናውኗል፡፡
- ❖ የባለስልጣኑን ህንጻ አንደኛ ወለል ለማስዋብና ለፕሮሞሽን አገልግሎት እንዲውል በታቀደው መሠረት የዲዛይን እንዲሁም የሲቪል ስራዎችና የእቃ ግዥ በመፈጸም ቦታው አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡
- ❖ እ.ኤ.አ በአፕሪል ወር ውስጥ በዩናይት ኪንግደም ለንደን በተቆላ ቡና ላይ በበይነ-መረብ ኮንፈረንስ ለማከናወን ከ11 በላይ ቡና ላኪዎችና ቡና በመቁላት ላይ ከተሰማሩ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ስለሚከናወነው የተቆላ ቡና የስራ እንቅስቃሴ እና ስለ ድርጅታቸው አጭር ማብራሪያ እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡
- ❖ በቻይና ሻንሀይ የሀገራችንን ቡና ለማስተዋወቅና የተሻለ ገበያ ትስስር ለመፍጠር በተደረገው ዌብናር በመላክ ላይ ያሉ 27 ቡና ላኪ አርሶ አደሮች መረጃ የተላከ ሲሆን በቻይና በኩል በቀሪ ወራት ከ 6ሺ ቶን ቡና ለመግዛት፣ በብራንድ ዲቨሎፕመንትና ምዝገባ ዙሪያ እንዲሁም ለጅማ ሪሰርች ሴንተር ድጋፍ ለማድረግ ስምምነት ቃል ተገብቷል ፡፡
- ❖ በዱባይ የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ (GULF food trade fair )በተካሄደው ኤግዚቢሽን እና ባዛር ደረገው 24 ድርጅቶች እንዲሳተፉ የተደረገ ሲሆን የማስተዋወቅና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡
- ❖ በ2012 በጀት ዓመት የቡና ፣ ሻይ እና ቅ/ቅመም ምርቶችን በመላክ ከፍተኛ አፈጻጸም ያሳዩ ላኪ ድርጅቶችን ማበረታቻና እውቅና ተሰጥቷል፡፡
- ❖ ‹‹Future Tea and Coffee Specialty Summit and Expo›› በሚል በቡናና ሻይ ላይ የሚያተኩር ቨርቹዋል ኤክስፖ እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 13 በሲንጋፖር ተካሄዶ.ል በዚህ ዝግጅት ላይ ቡና ላኪዎቻችን መሳተፍ እንዲችሉ የማስተባበር ስራ ተሰርቷል፡፡

❖ ካንቤራ የሚገኘው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ የሀገራችንን ምርቶች ለማስተዋወቅና የገበያ ዕድል ለማስገኘት ይረዳ ዘንድ ለማሳያ የሚሆኑ የቡና ናሙናዎች እንዲላክላቸው በጠየቀው መሰረት የሀገራችንን ቡና ለማስተዋወቅ የሚረዳ ከዋና ዋና የቡና አይነቶች ለማሳያ የሚውል የቡና ናሙና ተዘጋጅቶ እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

**የምርት አቅርቦት ማሻሻል**

በግብይት ማዕከላት፡-በ2013 በጀት ዓመት 273,926.10 ቶን ቡና ወደ ምርት ገበያ የቀረበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 68,641.17 ቶን በተለያዩ የግብይት አማራጮች በምርት ገበያ ደረጃ ወጥቶለት ወደ ኤክስፖርት ቡና ማዘጋጃ የተጓጓዘ ነው፡፡ ከቀረበው ቡና ውስጥ 128,444.56 ቶን በተለያዩ የግብይት አማራጮች (በህ/ሥ/ማ/ዩኒየን 18,097.90 ቶን (6.6%)፣ በአልሚ ላኪ 8,940.12 ቶን (3.26%)፣ በቀጥተኛ ትስስር 101,406.54 ቶን (37.08%) በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደረጃ ወጥቶለት ወደ ኤክስፖርት ቡና ማዘጋጃ የተጓጓዘ ሲሆን ቀጥታ ለምርት ገበያ በአቅራቢዎች 145,481.54 ቶን (53.1%) ለገበያ ቀርቧል ፡፡

በቡና አዘገጃጀት፡- በ2013 በጀት ዓመት ከቀረበው ቡና ለወጭ ገበያ የሚቀርብ ያልታጠበ 171,577.48 ቶን(57.17%)፣ ለወጭ ገበያ የሚቀርብ የታጠበ 82,918.11 ቶን (27.63%)፣ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚቀርብ ያልታጠበ 25,503.60 ቶን(8.5%)፣ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የታጠበ 20,068.84 ቶን(3.69%)፣ በአጠቃላይ ያልታጠበ (ለወጭ እና ለሀገር ውስጥ) የቀረበው 197,081.07 ቶን (65.66%) ፣የታጠበ (ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ) 102,986.96 ቶን (34.31%) እና በከፊል የታጠበ 65.64 ቶን (0.02%) ድርሻ አላቸው፡፡

**የቡና ክምችት ክትትልና ቁጥጥር**

በ2013 እቅድ ዘመን የወጪ ቡና ክምችትና ቁጥጥር አንድ ጊዜ ድንገተኛ የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘኖች ላይ ለማድረግ ታቅዶ አንድ ጊዜ/100%/ ተደርጓል፡፡ ቁጥጥሩ 50%/ ኢንደስትሪዎች በመሸፈን የ2010 ምርት የሆነ ቡና 347.5 ቶን እና 3,750.90 ቶን ቡና መኖሩ ተረጋግጦ ወደ ውጪ እንዲላክ ተደርጓል፡፡

በምልከታው በርካታ ኢንዳስትሪዎች የተደራጀ የክምችት መረጃ አያያዝ ስርአት የሚከተሉ መሆኑ፣ የምርት አያያዝና አከመቻቸት በንጽህና የተጠበቀ መሆኑ፣ በአብዛኛዉ የማዘጋጃ ኢንዳስትሪዎች የሚገኝ የቡና ክምችት የሽያጭ ኮንትራት የተገባለት መሆኑ፣ ካለፉት

አመታት አንጻር በመጋዘን የተገኘው የከረመ ምርት መጠን እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ፤ በሁሉም ኢንዳስትሪዎች የምርት የክምችት መመሪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የጀመሩት ጥረት አበረታች መሆኑ ታይቷል፡፡

**የህገ - ወጥ ቡና ዝውውርና ንግድ ቁጥጥር**

ህገወጥ ቡና ቁጥጥርን በተመለከተ በክክሎች እና ባለስልጣኑ በሚቆጣጠራቸው ኬላዎች 3691.8 ቶን የቡና ምርት በህገ-ወጥ መንገድ ሲንቀሳቀስ ተይዞ እሰካሁን ለሽያጭ ከቀረበዉ ምርት 58,167,500 ብር ገቢ ተገኝቷል፡፡

**የመረጃ ትንተናና ስርጭት**

በ2013 በጀት ዓመት የአገር ውስጥ ግዥ እና የኤክስፖርት ዋጋ ንጽጽር ለመስራት በታቀደው መሰረት እስካሁን 10 ጊዜ ተሰርቶዋል፣ የገበያ መረጃ ማሰባሰብ፣ ማደረጃት መተንተን እና ለተጠቃሚው በተፈለገው አግባብ ማሰራጨት የሚያስችል አንድ ዳታ ቤዝ እና ሲስተም ሶፍት ዌር ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት ስራዉ ተጠናቆ የማስጀመሪያ ሙከራ ላይ ይገኛል፡፡

**የቡና ሽያጭ ውል/ኮንትራት አስተዳደር**

የቡና ኮንትራት አስተዳደር መመሪያ ጽድቆ ወደ ተግባር ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እለታዊ የቡና ዋጋ መተንተን በመጀመሩና ቁጥጥር በመጠናከሩ ቡናችን የሚሸጥበት አማካይ ዋጋ ማሳደግ ተችሏል። በመሆኑም በአመቱ የተላከ ምርት መጠን የቀነሰ ቢሆንም በዋጋ ጭማሪ ማስመዝገብ ተችሏል።

**የቅንጅታዊ አሰራርን ማሳደግ**

- ኤስፖርቱ በቀጥታ ከሚመለከታቸዉ መ/ቤቶች የተውጣጣ አንድ ቅንጅታዊ ኮሚቴ በቡናና ሻይ ባለሥልጣን ሰብሳቢነት በሳምንት ዉስጥ ኤክስፖርቱን በተመለከተ የተከናወኑትን ተግባራት በመገምገም ለተፈጠሩት ችግሮች ደግሞ የመፈትትሂ አቅጣጫ በማስቀመጥ ለሥራዉ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ተደርጓል፣

- ከጉምሩክ ኮሚሽን ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጋር በዱከም በርና ከቱሉ ዲመቱ ቡና ቁጥጥር ኬላዎች ጋር በቅንጅት የሚሰሩበት ሁኔታ ውይይት በማድረግ ምቹ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር ተደርጓል፣
- የክትትልና ድጋፍ ሥራውን በመረጃ የተደገፈ በማድረግ ኮንትራት ኖሯቸው ያልላኩ፣ ኮንትራት ሳይኖራቸው ቡና በእጃቸው ያላቸውን በመለየት ድጋፍ ማድረግ በመቻሉ በራሳቸው ገበያ እንዲያፈላልጉ ካልቻሉም በራሳቸው ስምምነት መነሻ ቡናውን በመቀበባበል ወደ ውጪ እንዲልኩ በላኪዎች መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር በማደረግ ከ2,419 ቶን በላይ ቡና ወደ ውጪ በወቅቱ እንዲላክ ማድረግ ተችሏል፡፡
- በ2012 በጀት ዓመት የባለ ልዩ ጣዕም ቡና ውድድር ላይ አሸናፊ ከሆኑ አርሶ አደሮች ጋር የውይይት መድረክ እና ለአሸናፊ አርሶአደሮች የዕውቅና አሰጣጥ የተደረገ ሲሆን ውድድሩም እንዲሳካ ከፍተኛ ጥረት ላደረጉ ተቋማትና ግለሰቦችም እውቅና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡
- በሀገራችን ለሁለተኛ ጊዜ እየተካሄደ ላለው አለም ዓቀፍ የልዩ ቡና ቅምሻ ውድድር /Cup of Excellence/ በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ ከFeed the Future Value Chain Activities ጋር በመተባበር በ 3 ማስተባበሪያ ውስጥ በሚገኙ 9 የግንዛቤ መስጫ ማዕከላት በልዩ ቅምሻ ውድድር እና ድህረ-ምርት ላይ በአጠቃላይ ለ2,073 ተሳታፊዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- የማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም የቡና ሻይ እና ቅመማ ቅመም ምርቶችን ለማስተዋወቅ የገበያ ትስስር ሊፈጥር የሚያስችል የማህበራዊ መድረክ በመገንባት መረጃ የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡
- የተባበሩት መንግስታት የንግድና የልማት ጉባኤ በሀገራችን እሴት የተጨመረበትን የቡና ግብይት ሰንሰለት ለማጠናከር እና ኤክስፖርቱን ለማሳደግ ይረዳል የተባለ ፕሮጀክት ቀርጾ ጥናት ሲያካሂድ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በዚህም ከፕሮጀክቱ አስተባባሪዎች ጋር አስፈላጊውን መረጃ የመለዋወጥ እንዲሁም በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የመሰብሰቢያ አዳራሽ መጋቢት 11 ቀን 2021 በተደረገው የማጠቃለያ የፕሪጀክት ዎርክ ሾፕ ስኬታማ እንዲሆን የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና በዘርፉ ላይ የተሰማሩት የግብይት ተዋንያን እንደሳተፉ ጥሪ በማድረግ የማስተባበር ሥራ ተከናውኗል፡፡

- ዓለም ዓቀፍ የቡና ግብይት /Global Coffee Marketing/፣ የቡና ግብይት ስትራቴጂ /Coffee Marketing Strategies/ የኤክስፖርት አሰራርና ኮንትራት አስተዳደር እንዲሁም ብራንዲንግ ላይ ደረጃውን የጠበቀ የሀገር ውስጥ ስልጠና ለባለስልጣኑ ግብይት ባለሙያዎች እና ለላኪዎች ተሰጥቷል፡፡
- የቡና ሻይ እና ቅመማ ቅመም ግብይቱን በተሻለ ሁኔታ ለመደገፍ ከባለድርሻ አካላት ጋር 2 ጊዜ የምክክር መድረክ ተከናውኗል፡፡

**የአሠራር ስርዓቶችን ማሻሻል**

- የኮንትራት አስተዳደር መመሪያ ከአዋጅና ደንብ እንዲሁም ከብሔራዊ ባንክ አሰራር ጋር ለማጣጣም መመሪያ ተዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ተደርጓል፣
- በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ላይ ቡና ተዋናዮች ባቀረቡት ቅሬታ መሰረት ለመፍታ የሚያግዝ የአሰራር መሻሻያዎች ተጠንቶ ተግባራዊ ተደርጓል፤

# 7. የ2014 ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች

## 7.1. ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ

የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርትና ምርታማትን ለማሳደግ የምንከተለው የአመራረት ስርዓት በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች፣ መካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት እርሻዎችን መሰረት አድርጎ የሚለማ ይሆናል፡፡ በዕቅዱ የተካተቱ ቡና፤ ሻይ እና በሃገር ደረጃ ኤክስፖርት ተኮር ተብለዉ የተለዩ 11 ቅመማ ቅመም ሰብሎችን ማለትም በርበሬ፣ ዝንጅብል፣ ኮረሪማ፣ እርድ፣ አዝሙድ፣ አብሽ፣ ድምብላል፣ ቁንዶ በርበሬ፣ ጥምዝ፣ ሮዝመሪ እና ሚጥሚጣ) በዕቅዱ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

**ቡና**

በሁሉም የአመራረት ስርዓቶች የቡና ምርትን ከ680 ሺህ ቶን ወደ 708 ሺህ ቶን ከ7.5 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 7.6 ኩ/ል/ሄ/ር ለማድረስ ታቅዷል፡፡

**ሻይ**

ለሰፋፊ የሻይ እርሻዎች እና በአውት ግሮወር ለታቀፉ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው የሻይ አምራች አርሶ አደሮች ድጋፍና ክትትል በማድረግ የሻይ ምርትን ከ 11.4 ሺህ ቶን ወደ 11.95 ሺህ ቶን እንዲሁም ምርታማነትን በሻይ ልማት ድርጅቶች 37 ኩ/ሄ/ር ወደ 38.5

ኩ/ሄ/ር እና በአዉትግሮወር ከ23 ወደ 24.3 ኩ/ሄ/ር በማድረስ አማካይ ምርታማነት ከ 35 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 36 ኩ/ል/ሄ/ር ለማድረስ ታቅዷል፡፡

**ቅመማ ቅመም**

በዋና ዋና የቅመም ምርቶች የሚሸፈን መሬት በማሳደግ ምርቱን ከ644.3 ሺ ህ ቶን ወደ 705.14 ሺ ህ ቶን ለማድረስ እንዲሁም ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ በተመረጡ ቅመማ ቅመሞች በርበሬ ከ 15.3 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 18.7 ኩ/ል/ሄ/ር፣ ደረቅ ዝንጅብል ከ 28.4 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 29 ኩ/ል/ሄ/ር፣ ኮረሪማ ከ 7 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 7.6 ኩ/ል/ሄ/ር፣ እርድ ከ 39.7 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 40 ኩ/ል/ሄ/ር ፣ ጥቁር አዝሙድ ከ16.4 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 16.5 ኩ/ል/ሄ/ር፣ ነጭ አዝሙድ ከ9.5 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 9.9 ኩ/ል/ሄ/ር፣ አብሽ ከ11.7 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 12.1 ኩ/ል/ሄ/ር፣ ጥምዝ ከ 5 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 5.1 ኩ/ል/ሄ/ር፣ ድንብላል ከ 15.8 ወደ 16 ኩ/ል/ሄ/ር ፣ ሮዝመሪ በዕርጥብ ከ10 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 15.6 ኩ/ል/ሄ/ር፣ ሚጥሚጣ ከ9.4 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 10.6 ኩ/ል/ሄ/ር እና ቁንዶ በርበሬ ከ11.2 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 12 ኩ/ል/ሄ/ር ምርታማነት በበጀት ዓመቱ ተደራሽ ለማድረግ ግብ ተቀምጧል፡፡

ይህም የምርታማነት ደረጃ የተወሰደው የተሻሻለ ቴክኖሎጂን ተጠቃሚ ሞዴል አርሶ አደሮች በ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ ዘመን አፈጻጸም ላይ የደረሱበትን የሁሉም አርሶ አደሮች ሀገር አቀፍ አማካይ እንዲሆን የሚያስችል ከፍተኛ ጥረት በሁሉም የባለድርሻ አካላት እንደሚደረግ በታሳቢነት ተወስዶ ነው፡፡

## 7.2. የወጪ ንግድን በመጠንና በገቢ ማሳደግ

**ቡና**

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ እንደ ሀገር የሚወሰድ መረጃ ስለሆነ ይህንን መረጃ በመውሰድና ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ወደ ውጭ የተላኩትን የምርት መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ከ2013 በጀት ዓመት ወደ 2014 በጀት ዓመት ልሸጋገር የሚችል 130,000 ቶን ቡና ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም የተመረጠውን የትንበያ ሞዴል በመጠቀም በ2014 በጀት ዓመት ለውጭ ገበያ የሚቀርበው የቡና ምርት ጠቅላላ መጠን 280 ሺ ህ ቶን እንደሆን ታቅዷል፡፡ ይህን መጠን ለውጭ ገበያ በማቅረብ 1.014 (አንድ ቢሊየን አስራ አራት ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማስገኘት ግብ ተጥሏል፡፡

**ቅመማ ቅመም**

ወደ ወጪ የተላካው የቅመማ ቅመም ዓይነት ዝርዝር በርካታ ቢሆንም መጠናቸው ግን አነስተኛ በመሆናቸው የባለሙያን የምርት፣ የአቅርቦትና የወጪ ንግድ አፈጻጸም ሂደት መረጃ ትንተናን መሰረት በማድረግ በ2014 በጀት ዓመት 14,028.8 ቶን ምርት ወደ ውጭ በመላክ 17.24 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማስገኘት ግብ ተጥሏል፡፡

**ሻይ**

የባለስልጣኑን የሁለት ዓመታት ተከታታይ ወሪሃዊ አፈጻጸም መረጃዎችን መሰረት በማድረግና የትንበያ ሞዴሉን በመጠቀም በ2014 በጀት ዓመት ለውጭ ገበያ የሚቀርበው ሻይ ምርት 1,922.02 ቶን ሲሆን የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ግኝት 3.07 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚሆን ተሰልቶ ታቅዷል፡፡

በአጠቃላይ በ 2014 በጀት ዓመት **295,951.17** ቶን የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት ለዓለም ገበያ እንዲቀርብ በማድረግ **1.035** ቢሊየን ዶላር ገቢ ለማስገኘት ይሰራል፡፡

### 7.3. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

**የሴቶችና የወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ**

የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ንዑስ ዘርፍ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሃገራችንን 25 በመቶ ህዝብ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ በተለይ የሴቶችና ወጣቶች የሥራ አጥነት ችግር በመቅረፍ ረገድ ከችግኝ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ወጪ ንግድ ባሉ ደረጃዎች ሰፊ ዕድል መፍጠር ይቻላል፡፡ ስለሆነም የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ስልቶችን በመንደፍ በምርት ስብሰባና ዝግጅት፣ በአቅርቦትና በኤክስፖርት ምርት ዝግጅት እና በዕሴት ጭመራ እንዲሁም በቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት የተሰማሩ ባለሃብቶች የተለያዩ ማሳ እንክብካቤ ስራዎች በጊዚያዊ ስራ እድል በመፍጠር እና በማጠናከር በቋሚነት ወንድ 10629 ሴት 5333 በድምሩ 15962 እና በጊዚያዊ የስራ እድል ወንድ 63,661 ሴት 47,128 በድምሩ 110,789 የሥራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚነታቸውን የማሳደግ ስራ በትኩረት ይሠራል፡፡

- በሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ላይ የተሰራ አንድ የዳሰሳ ጥናት ይካሄዳል
- የስርዓተ-ፆታ እኩልነት ስትራቴጂክ ሰነድ ዝግጅት ማጠናቀቅና ሰነዱን ተግባራዊ ማድረግ

- በስርዓተ ጾታ አተገባበር እና በወጣቶች የስራ እድል ፈጠራ ላይ የተሰሩ ምርጥ ተሞክሮዎችን መለየትና መቀመር
- የሴቶችና ወጣቶች  የስራ እድል ፈጠራ ማካተት ስራዎች ላይ ከክልሎች ለተወጣጡ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት

በሁሉም የሥራ ክፍሎች የሴቶችና  ወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ጉዳይ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡ ወጣቶትና ሴቶች በዘርፉ በሚፈጠሩ ጊዚያዊ የሥራ ዕድሎች በመጠቀም ለቋሚ የሥራ ዕድል ፈጠራ መነሻ ካፒታል እንዲያገኙ ከክልሎች  ጋር በቅንጅት ይሠራል፡፡

## 8. የዕቅዱ ማስፈፀሚያ ስልቶች

### 8.1. ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚከናወኑ ተግባራት

#### 8.1.1. የኤክስቴንሽን ተደራሽነት ማስፋፋት

በበጀት ዓመቱ የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ኤክስቴንሽን ስርዓት 5.75 ሚሊዮን አርሶ አደሮች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ያደርጋል፡፡ ከእነዚህ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች ውስጥ 20 በመቶ የሙሉ ፖኬጅ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ካሉት የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች ውስጥ  አዳዲስና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን የሚቀበልና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገብሩ እንዲሁም ለሌሎች አርሶ አደር አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ 10 በመቶ ሞዴል አርሶ አደሮችን መፍጠር ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል፡፡ በቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት ሥራ ከተሰማሩ ዉስጥ እማወራዎችን 100%፣ ባለትዳር ሴቶች 50%፣ እንዲሁም 10 በመቶ የሚሆኑትን ወጣቶች የቡና ሻይ እና ቅመማ ቅመም ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ይደረጋሉ፡፡

#### 8.1.2. የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ማሳ እንክብካቤ ስራዎች

**ቡና ዕደሳ**

አብዛኛው ቡና በእርጅና ምክንያት ከመዳከሙ የተነሳ በቡና ምርትና ምርታማነት ላይ እያደረሰ ያለዉን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ  በበጀት ዓመቱ 77,234 ሄ/ር በጉንደላ፣ 55,633 ሄ/ር  ነቅሎ በአዲስ  በመተካት በድምሩ 132,867 ሄ/ር የቡና ማሳ ለማደስ

ታቅዷል፡፡ በዚህ ስራ ላይም 1,492,070 ወንድ እና 228,987 ሴት  በድምሩ 1,721,057, ተሳታፊ አርሶ አደሮች ይሳተፋሉ፡፡

**ደጋፊ መስኖ**

የዝናብ መጠንና ስርጭት መዛባት ባለባቸው አካባቢዎች በአበባና በፍሬ መሙላት ወቅት የቡናው ተክል የሚያስፈልውን የውሃ መጠን እንዲያገኝ ለማድረግ ደጋፊ መስኖ አስፈላጊ በመሆኑ በ2014 ዓ.ም 24,364 ሄ/ር የሚለማ ሲሆን በዚህም ስራ 87,711 ወንድ እና 9,746 ሴት በድምሩ 97,457  አርሶ አደሮች ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

**የደባል ሰብሎች ልማት**

ከቡና ልማት ጋር በተጓዳኝነት በማምረት ለአርሶ አደሩ ተጨማሪ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ ደባል ሰብሎችን መጠቀም ተመራጭ ነው፡፡ በመሆኑም በ2014 በ159,011 ሄ/ር ላይ ከቡና ጋር በደባልነት በመጠቀም እንዲለሙ ይደረጋል፡፡

ደባል ሰብሎች የቡናውን የወደፊት ዕድገትና ምርት ሳይጎዱ የመሬቱን ምርታማነት ከመጨመር ባሻገር አረምን በመቆጣጠር፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የአፈሩን ለምነት ለማሻሻል፣ ለእንስሳት መኖነት የሚሆኑ እንደ ሰስባኒያ እና ዲስሞዲየም የመሳሰሉትን በ2014 ዓ.ም በ2,266 ሄ/ር ላይ ከቡና ጋር በተጓዳኝነት ለማልማት ታቅዷል፡፡

**ዘርፈ-ብዙ ጠቀሚታ ያላቸው የጥላ ዛፎች ልማት**

ከቡና ጋር በተጓዳኝ ሊለሙ የሚችሉ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው የጥላ ዛፎችን በ2014 ዓ.ም በ17,597 ሄ/ር ላይ በምክረ-ሃሳቡ መሰረት ከቡና ጋር በተጓዳኝነት ለመትከል ታቅዷል፡፡

በአጠቃላይ በደባል ሰብሎች ልማት፣የተጓዳኝ የእንስሳት ሀብት ልማት እና  የተጓዳኝ የእንስሳት ሀብት ልማት ስራዎች ላይ 322,026 ወንድ እና 35,780 ሴት በድምሩ 357,806 አርሶ አደሮች ተሳታፊ ይሆናል፡፡

### 8.1.3. በሽታና ተባይ መከላከልና መቆጣጠር

**የቡና ፍሬ በሽታ መከላከል**

የቡና ፍሬ በሽታ በቡና ምርት፣ ምርታማነትና ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከሚያደርሱ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህን በሽታ ለመከላከል ዋነኛው መፍትሄ በምርምር የተረጋገጡና በሽታውን መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎችን መጠቀም ቢሆንም ምርት እየሰጡ ያሉ የአካባቢ ዝርያዎችን በዓመት 4 ዙር በ110,000 ሄ/ር የማሳ አሰሳ በማድረግ የበሽታውን ስርጭት ለመከላከል የቡና ምቀሳና እንክብካቤ ስራዎች እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

### የቡና ግንድ አድርቅ በሽታ መከላከል

የቡና ግንድ አድርቅ በሽታን ለመከላከል ባሕላዊ የመከላከያ ዘዴዎችን (ሽፋን ሰብሎችን፣ ጉዝጓዝ እና ጸረ-አረም ኬሚካል) በመጠቀም የቡና ግንድ አድርቅ በሽታን የመተላለፍ አቅም የመቀነስ ሥራ እንዲተገበር ይደረጋል፤ በተጨማሪም ለቡና እንክብካቤ ሥራዎች የምንጠቀማቸዉን የእርሻ መሳሪያዎቸ በሽታዉን ከሚያመጡ ተህዋስያን የጸዱ ማድረግና የቡናን ግንድ አድርቅ በሽታ መስፋፋትን ለመቀነስና ለመቆጣጠር 4 ዙር የማሳ አሰሳ በማድረግ በበሽታው የተጠቁ 3,500,000 የቡና እግር ዛፎችን ነቅሎ በማቃጠል ለማስወገድ ታቅዷል፡፡

በተጨማሪም የበሽታው ጥቃትና ጉዳት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ማወቅ በሽታውን ለመከለከልና ለመቆጣጠር ወሳኝ በመሆኑ በ2014 በጀት ዓመት ሁለት ዙር የቡና ግንድ አድርቅ በሽታ አሰሳ ጥናት ለማካሄድ ዕቅድ ተይዟል፡፡

### የቡና ቅጠልና ቅርንጫፍ ለብላቢ በሽታ መከላከል

በሽታው በሲዳማ ክልል እና በደቡብ ክልል ጌዴኦ ዞን የተወሰኑ ወረዳዎች የቡናን ምርት በመቀነስ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በዓመት 4 ዙር አሰሳ በማድረግ በበሽታው የተጎዱ ቅርንጫፎችን መመቀስና ማቃጠል፣ የእርሻ መሳሪያዎችን በአልኮል የማጽዳት እና ሌሎች የቡና እንክብካቤ ስራዎች እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡

### የሻይ ሰብል ጥበቃ ስራዎች

በሃገራችን የሻይ ልማት እስካሁን በስፋት ያለተሰራበት ቢሆንም ባለው ውስን የሻይ ልማት ላይ የሚከሰቱ ተባይ፣ በሽታና አረም መከላከል ስራዎች አቅም በስልጠና ለማሳደግና ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዷል፡፡

**የቅመማ ቅመም ሰብል ጥበቃ ስራዎችምርትና ምርታማነትን በተሻለ ሁኔታ ለማሳደግ**

የቅመማ ቅመም በሽታና ተባይ ቁጥጥር ጅምር ሥራዎችን አጠናክሮ ከማስቀጠል በተጨማሪ አስፈላውን 2 ዙር ስልጠናና 4 ዙር ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዷል፡፡

**የበርበሬ በሽታ መከላከል**

የበርበሬ ሰብልን ከተባይና በሽታ ለመከላከል በርበሬ የሚለማበትን ማሳ አስቀድሞ የማፅዳት ስራ፣የሰብል ፈረቃ፣የውሀ ማፋሰሻ ስራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ በ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት 4 ዙር የበርበሬ ሰብል ማሳ ላይ የተባይና በሽታ አሰሳና የመከላከል ስራ ይከናወናል፡፡

**የዝንጅብል አጠውላጊ በሽታን መከላከል**

የዝንጅብል ቅመምን ከተባይና በሽታ ለመከላከል ዝንጅብል የሚለማበትን ማሳ አስቀድሞ የመለየት፣የሚለማበትን ወቅትና ቦታ የመወሰን ስራ፣ለአጠውላጊ በሽታ የሚያጋልጡ ሁኔታዎች እንዳይኖሩ የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ በ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ዝንጅብል በስፋት በሚለማባቸው ክልሎች ባሉ ወረዳዎች 4 ዙር የዝንጅብል አጠውላጊና ሌሎች በሽታ ጥቃት አሰሳና የመከላከል ስራ ይከናወናል፡፡

**የዕርድና በርበሬ ድህረ-ምርት ዝግጅት**

የዕርድና የበርበሬ ምርት በአፍላቶክሲን ምክንያት በውጭ ሀገር ገበያ ላይ ተቀባይነታቸው እየቀነሰ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ደቡብ እና አማራ ክልሎች በሁለት ማዕከላት የምክክር መድረክ በማዘጋጀት በቁጥር 250 ለሚሆኑ ባለሙያዎች፣ አርሶ አደሮች፣ ነጋዴዎች እና ባለድርሻ አካላት ሥልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይት ይደረጋል፡፡

**8.1.4. የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ማሳ ሽፋን ማሳደግ**

**የቡና ማሳ ሽፋን ማሳደግ**

ቡናን ስፔሻላይዝ ባደረጉና ነባር የቡና አካባቢዎች የሚገኙ የቡና አምራች አርሶ አደሮች ባላቸው የእርሻ መሬት ላይ ለቡና ልማት ምቹ ሁኔታዎችን (አስቀድሞ ጥላ ዛፍ በመትከል፣ አልሚ ሰብሎች በማልማት) የቡና ማሳ የማስፋት እንዲሁም ቡና የሚያለሙ አዳዲስ አርሶ አደሮችን ግንዛቤ በማስጨበጥና በመደገፍ ወደ ልማቱ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ስነ-ምህዳርን መሰረት ባደረገ መልኩ በጥናት ላይ ተመስርቶ ለቡና ተስማሚ የሆኑ አዳዲስ አካባቢዎችን በመለየት ቡናን በስፋት እንዲያለሙ የተሻሻሉ የቡና

ዝርያዎችን በማቅረብና በምክረ-ሃሳቡ መሰረት በመጠቀም ውጤታማ እንዲሆኑ የተሻለ ክትትልና ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በዚህም አዲስ ለቡና ልማት ተስማሚ በሆነ መሬት ላይ በተያዘዉ በጀት ዓመት አዲስ ተከላ 115,200 ሄ/ር፤በሞተ ከዳ በቁጥር 181,440,000 እና ስግሳጎ በቁጥር 46,080,000 ተከላ ለማካሄድ ታቅዷል፡፡ እንዲሁም ነባር ምርት የቀነሱ ቡናዎችን እደሳ በማድረግ ጠቅላላ የቡና ማሳ ሽፋንን ከነበረበት 1,136,892 ሄ/ር ወደ 1,372,092 ሄ/ር እና ምርት የሚሰጥ የቡና ማሳ 931,727 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዷል፡፡

### የሻይ ማሳ ሽፋን ማሳደግ

የሻይ ልማት በተመለከተ ሰፋፊ የሻይ እርሻዎችን ለማስፋፋት የሚያስችል ቅድመ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ወደ ተግባር ማስገባትና በዙሪያቸው የሚገኙ አርሶ አደሮችን በስፋት በማቀፍ ምርቱን ማሳደግ የሚቻልበትን አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ለሻይ ልማት ተስማሚና ምቹ ስነ-ምህዳር ባላቸው አካባቢዎች አነስተኛ የሻይ ኢንዱስትሪዎች በሚስፋፉበት ሁኔታ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ስራ እጥ ወጣት በልማቱ የሚሳተፍበትን ዕድል በመፍጠር የሻይ ምርት ሽፋን የማሳደግ ሥራ ይሠራል፡፡ በዚህም የአነስተኛ እርሻ ማሳ ሽፋን በዓመቱ ከ635 ሄ/ር ወደ 726 ሄ/ር በማድረስ ምርት የሚሰጥ ሻይ ማሳ ሽፋን ከ483 ሄ/ር ወደ 501 ሄ/ር እንዲሁም የሰፋፊ እርሻ ምርት የሚሰጥ ማሳ ሽፋን በዓመቱ 2733 ሄ/ር ወደ 2788 ሄ/ር በማሳዳግ ጠቅላላ የሰፋፊ እርሻ ሻይ ማሳ ሽፋን ከ2810 ወደ 2865 እንዲያድግ በማድረግ በድምሩ የሻይ ማሳ ሽፋን አሁን ከሚገኝበት 3528 ሄ/ር ወደ 3591 ሄ/ር በማድረስ ምርት የሚሰጥ ሻይ ማሳ ሽፋንን ከ 3242 ሄ/ር ወደ 3289 ሄ/ር ለማድረስ ይሰራል፡፡

### የቅመማ ቅመም የማሳ ሽፋን ማሳደግ

የቅመማ ቅመም ልማት በተመለከተ የተቀናጀ ስራ በመስራት የመሬት ሽፋኑን ከ387 ሺ.ህ ሄ/ር በዓመቱ ወደ 397227.6 ሄ/ር ለማድረስ ይሰራል፡፡

የማሳ ማስፋት ሥራው የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት ፓኬጅ በማዘጋጀት በፓኬጁ አተገባበር ዙሪያ የስልጠናና የምክር አገልግሎት በመስጠት፣ የኩታ ገጠም /ክላስተር/ ልማት ሥራን በማስፋፋት እና የልማትና ግብይት ትስስር (Outgrowers Scheme) አሰራርን በማጠናከር የሚፈጸም ይሆናል፡፡

### 8.1.5. የተሻሻለ የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ግብዓት አቅርቦት ማሳደግ

### የዘር እና ችግኝ ዝግጅት

ለቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት የሚያስፈልጉ የዘርና የችግኝ አቅርቦትና ስርጭት፣ የዘመናዊ እርሻ መሳሪያዎች አቅርቦት፣ የማዳበሪያና የሌሎች ግብዓቶች አቅርቦት ሥርዓት የምርታማነት ዕድገት ግቡን ለማሳካት በሚያስችል ደረጃ አልነበረም፡፡ ስለሆነም የአርሶ አደር፣ የግል ባለሃብት፣ ሕብረት ሥራ ማህበራት እንዲሁም መንግስት በምርጥ ዘር፣ በማዳበሪያ በጸረ-ተባይ እና ሌሎች ግብዓቶች አቅርቦት እና ስርጭት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲሰፋ በማድረግ ነባርና አዳዲስ የዘር እና የችግኝ ማባዣ ቦታዎችን በማጠናከርና በማስፋፋት ዘመናዊ የግብዓት አቅርቦትና ስርጭት ስርዓትን በመዘርጋት ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡

የተሻሻሉ ግብዓቶች ከማምረት እስከ ተጠቃሚው የማድረስ ተግባራት ላይ የግል ዘርፉን ተሳትፎ በማጠናከር ባለፉት ጥቂት ዓመታት የታዩ ክፍተቶችን ሊቀርፍ የሚችል የግብዓት ግብይት ሥርዓት በመዘርጋት ግብዓቶች በአርሶ አደሮች ፍላጎት መሰረት እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

በአጠቃላይ የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ግብዓትን ጥራት ያለዉ ዘር በስፋት የማምረቱ ሥራ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ በተለይ የምርጥ ዘር ብዜት በዓይነትና በሚፈልግ መጠን እንዲቀርብ ታማኝ አርሶ አደሮች መሰረት ያደረገ የመነሻ ዘር እና የተመሰከረለት ዘር ብዜት ሥራ በስፋት ይከናወናል፡፡ ለግብዓት አቅርቦት መቀላጠፍ በዋናነት ትኩረት የሚሰጠው መረጃን በቀላሉ ተደራሽ ማድረግ የሚያስችል በበይነ መረብ የማስተሳሰር ሥራ ይሰራል፡፡ የሚቀርበው ግብዓት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን የፌደራል እና የክልል ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካላት በቅንጅት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

በመሆኑም የቡና ምርጥ ዘር አቅርቦት በ2014 በጀት ዓመት 2,545 ኩ/ል፣ በጅማ ግብርና ምርምር ማዕከል የሚዘጋጀውን የዲቃላ ቡና ችግኝ በ2013 ከነበረበት 5,550 በበጀት ዓመቱ 8,400 ችግኞችን እንዲዘጋጁ ማድረግ፣ የቡና ችግኝ 814,377,669 ፣ በአውት ግሮወርስ ትስስር ከሻይ አልሚ ድርጅቶች 983,826 የሻይ ችግኝ ማዘጋጀት እንዲሁም የዋና ዋና ቅመማ ቅመም ሰብሎች የተሻሻለ ምርጥ ዘር ዝርያዎች በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋም ወይም በተመረጡ የመንግስት ችግኝ ጣቢያዎች በመሞከር ውጤታማነታቸውን ለአርሶ አደር በማስተዋወቅ በቀጣይ ወደ ዘር ብዜት ለማስገባት ከተለያዩ ምርምር

ማእከላት የሚሰበሰቡ የተለያዩ የቅ/ቅመም ዝርያዎች በርበሬ 0.5 ኪ.ግ፣አዝሙድ 10 ኪ.ግ፣ አብሽ 10 ኪ.ግ እና ድምብላል 10 ኪ.ግ በድምሩ 30.5 ኪ.ግ ዘር ይዘጋጃል፡፡

የአፈር ለምነትን ለማሻሻል ኮምፖስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) 10,947,620 ቶን ይዘጋጃል፡፡

#### 8.1.6. የግብዓት አቅርቦት

**ለምርት ዝግጅትና ድህረ ምርት አያያዝ የሚያስፈልጉ ግብአቶች በሚመለከት**

የቡና ማድረቂያ ሽቦ ወንፊት (ቺክንዋየር) 25920 ካ.ሜ፤ ሜሽ ሽቦ 2160 ካ/ሜ፤ ሼድ-ኔት 27,216 ካ.ሜ፤ ብትን የቃጫ ጆንያ 632367 ካ.ሜ፤ መሸፈኛ ቢጫ ላስቲክ 25920 ካ.ሜ፤ የቃጫ ኬሻ ባለ100 ኪ.ግ 8348263 እና ባለ 50 ኪ.ግ 1189764፤ ቃጫ ባለ 60 ኪ.ግ 2776115፣ ቃጫ ባለ30/25 ኪ.ግ 83634 እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ ይህንን እቅድ ለማሳካት እና ከዚህ በፊት የነበሩ የጆንያ ስርጭትና ተደራሽነት ችግር ለመቅረፍ፡

- ሀገር ውስጥ ጆንያ በማምረት ላይ የሚገኙ ሶስት ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ ያለባቸውን የተለያዩ ችግሮች በመለየት በባለስልጣኑ መፈታት ያለባቸውን በመፍታት ሌሎች ባለድርሻ አካላት ከሆኑ የሚፈቱት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ፣
- ፋብሪካዎቹ ያመረቱትን ጆንያ ተደራሽ እንዲሆን በተለያዩ ቦታዎች ወኪል እንዲፈጥሩ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- የገበያ ሰንሰለቱ እንዲያጥር የማድረግ ስራ በመስራት፣
- ጆንያ ከውጭ ለማስገባት ለሚፍልጉ ላኪዎች የቫውቸር ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል የድጋፍ በማድረግ የጆንያ አቅርቦቱንና ስርጭት ችግሮቹን ለመፍታት ጥረት ይደረጋል፡፡

**ለችግኝ ጣቢያ ስራዎች የሚያገለግሉ ግብአቶች**

ውሃ ማጠጫ 10,80፣ ባለ ሶስት ጣት መኮትኮቻ 1989፣የእጅ ጋሪ 1080፣ አካፋ 2429 ፤ዶማ 2,247፣ፖሊቲዩብ ከረጢት ባ416 8189 ኩ/ል፣ እንዲቀርብ ፍላጎት የመፍጠር ግብአቶችን የመለየት እና በወቅቱ የማቅረብ ሥራ ይሰራል፡፡

**ለቡና ማሳ እንክብካቤ የሚያስፈልጉ ግብአቶች**

የአረጀ ቡና መጎንደያ መጋዝ 43600፣የመጋዝ ምላጭ 43600 ቅጥያ ማሳስያ መቀስ 30500፣ ገጀራ 1080፣ በሚቀርበው ፍላጎት መሠረት በወቅቱ ለማቅረብ አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡

**ለሰብልና ጥበቃ ስራዎች የሚያስፈልጉ ግብአቶች**

የኬሚካል መርጫ መሳሪያዎች 1080 ባለ 15 ሊ/ር ለማቅረብ በእቅድ ተይዘዟል፡፡

**በቡድን ለሚደራጁ ተጠቃሚዎች የሚቀርቡ ቀላል ማሽኖች**

የቡና ዘር የእጅ መፈልፈያ ማሽን 2 እና ሞተራይዝድ መጎንደያ መጋዝ 2 ለማቅረብ በእቅድ ተይዟል፡፡

**8.1.7. ድህረ ምርት ዝግጅት እና ጥራት አጠባበቅ አሴት ጭመራ**

**የቡና፣ ምርት ጥራት ማሻሻልና ደረጃ ማሳደግ**

የቡና ምርት ማዘጋጃና የጥራት ማሻሻያ ሥራዎች በአርሶ አደሮች፣ አልሚ ባለሀብቶችና የምርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ባለቤቶች በምክረ-ሀሳቡ መሰረት ተግባራዊ እንዲያደርጉና የተዘረጋውን በጥራት ላይ የተመሰረተ የእሸትና የጀንፈል ቡና የገበያ ዋጋ ክፍያ ሥርዓት እንዲተገበር በመከታተል በጥራት ተወዳዳሪ የሆነ የቡና ምርት አቅርቦትን በማረጋገጥ የአርሶ አደሩን፣ የንግዱን ህብረተ-ሰብ ገቢና የሃገራችንን የውጭ ምንዛሬ ግኝት ማሳደግ ይሆናል፡፡

በዚህም የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ ከተደረሰበት 135.5 ሺ.ህ ቶን ወደ 140 ሺ.ህ ቶን እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ የታጠበ ልዩ ቡና ጥራት ደረጃን በዓመቱ ከነበረበት 68 በመቶ ወደ 70 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተይዟል፡፡ ይህንን ለማሳካት፡-

- ✓ የምርት ማድረቂያ 25 ሚሊዮን ካሬ ሜትር ከሽቦ ወንፊት፣ ከአውድማና ከአካባቢ ቁሳቁስ ተሰርቶ በአግባቡ የማድረቅ ሥራ እንዲሰራ ወቅታዊ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡
- ✓ ካሉት በቁጥር 1,450 የታጠበ ቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 193 የቡና መፈልፈያ በተለያዩ ምክያቶች ወደ ሥራ ያልገቡና የማይሰሩ በመሆናቸዉ ከባለድርሻዎች ጋር በመመካከር ወደ ስራ እንዲገቡ ጥረት ይደረጋል፡፡

- ✓ ከታጠበና ከደረቅ አዘገጃጀት ውጪ ያሉ ዝግጅቶች (anaerobic, honey, carbonic) በተጋባዥ አሰልጣኝ የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፣
- ✓ ለኢንዱስትሪዎች የሚቀርበው ቡና በምክረ-ሀሳቡ መሰረት በጥራት ተለቅሞ በወቅቱ እንዲዘጋጅ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ይሰጣል፣ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፤
- ✓ የተዘረጋው ጥራትን መሰረት ያደረገ የቀይ እሸት ቡና የዋጋ ክፍያ መመሪያ ተግባራዊ በሚደረግበት ላይ ከሚመለከታቸው ጋር ይሰራል፣
- ✓ በጥራት ማሻሻያ ግብዓቶች አቅርቦትና አጠቃቀም ላይ ከሚመለከታቸው ጋር ይሰራል፤
- ✓ በምርት ዝግጅት ላይ ከሚሰሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
- ✓ በታጠበ ቡና ቅድመ-ዝግጅት ወቅት በመስክና በተለያዩ አማራጮች ድጋፍና ክትትል ሥራ ይሰራል፡፡

ያልታጠበ ቡና ዝግጅት በ2013 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 408 ሺህ ቶን ጀንፈል ቡና 196 ሺህ ቶን ቅሽር ቡና ዝግጅት በ2014 ወደ 1001 ሺህ ቶን ጀንፈል ቡና በመሰብሰብ 480.58 ሺህ ቶን ቅሽር ቡና ለማዘጋጀት ታቅዷል፡፡ በዚህ መሰረት ልዩ ያልታጠበ ደረቅ ቡና ደረጃ ድርሻን ከ 11 በመቶ ወደ 12 በመቶ ለማሳደግ እና ያልታጠበ ደረቅ ቡና ዝቅተኛ ደረጃ ድርሻን ከ 7 በመቶ ወደ 6.5 በመቶ ለመቀነስ ግብ ተይዟል፡፡ ግቡን ለማሳካት፡-

- ✓ ካሉት 944 የደረቅ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 268 ማበጠሪያ ኢንዱስትሪዎች በተለያየ ምክንያት ወደ ሥራ ያልገቡና የማይሰሩ በመሆኑ ወደ ሥራ እንዲገቡ ከክልሎችና ከሌሎች ባለድርሻዎች ጋር ይሰራል፣
- ✓ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ውስንነትን በመለየት በተግባር የተደገፈ የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፤
- ✓ ለኢንዱስትሪ ኦፐሬተሮች በተጋባዥ ባለሙያ በተግባር የተደገፈ ሥልጠና ይሰጣል፤
- ✓ በመስክ፣ በአካልና በሪፖርት ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤
- ✓ የጀንፈል ቡና ጥራት ደረጃን መሰረት ያደረገ የዋጋ ክፍያ እንዲጠናከር ይሰራል፤
- ✓ በምርት ዝግጅት ላይ ከሚሰሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

- ✓ በደረቅ ቡና ማዘጋጃ ቅድመ-ዝግጅት ወቅት በመስክና በተለያዩ አማራጮች ድጋፍ ይደረጋል፡፡

**የቅመማ ቅመም ምርት ጥራት ማሻሻልና ማሳደግ**

ለቅመማ ቅመም ምርት ዝግጅትና ጥራት ልዩ ትኩረት በመስጠት የሚስተዋሉ ማነቆዎችን በመለየትና በመፍታት የአርሶ አደሩን እና የሃገራችንን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መስራት ይጠበቅብናል፡፡ በመሆኑም የቅመማ ቅመም ምርት ዝግጅትን በተመለከተ በ2013 የተደረሰበት 629.8 ሺህ ቶን ምርት እና 60.1 ሺህ ካሬ ሜትር ማድረቂያ በ 5 በመቶ በማሳደግ በ2014 በጀት ዓመት 661.2 ሺህ ቶን የቅመማ ቅመም ምርት በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለማዘጋጀት 63 ሺህ ካሬ ሜትር ማድረቂያ ከሸቦ ወንፊት፣ አውድማና ከአካባቢ ቁሳቁስ ተሰርቶ በአግባቡ የማድረቅ ሥራ እንዲሰራ ወቅታዊ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ግብ ተይዟል፡፡

**የሻይ ምርት ጥራትን ማሳደግ**

የሻይ እርሻ ልማት ድርጅቶች በሚገኙበት ዙሪያ የሚገኙና በሻይ ልማት የተሰማሩ አርሶ አደሮች የሚያቀርቡትን የሻይ ቅጠል የጥራት ደረጃ በምክረ-ሃሳቡ መሰረት እንዲሆንና አርሶ አደሮችም በቀጣይነት ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ ይሰራል፡፡ ስለሆነም በሻይ ልማት ድርጅቶችና በሻይ አልሚ አርሶ አደሮች የተዘጋጀ የሻይ ምርት በ2013 ከተደረሰበት 11.43 ሺህ ቶን ወደ 11.95 ሺህ ቶን ለማድረስ ግብ ተይዟል፡፡

**እሴት ጭመራ**

የቡናና ቅመማ ቅመም ምርቶችን ዕሴት በመጨመር ለዓለም ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ገቢን የመሳደግ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ተግባር ሲሆን ለዚህም በዘርፉ የተሰማሩና በቀጣይ በዘርፉ መሰማራት ለሚፈልጉ ድርጅቶች ተገቢዉን ድጋፍ በማድረግ የተዋንያኑን ተጠቃሚነትና የሀገሪቱ የውጪ ምንዛሬ ገቢ እንዲያድግ ይሰራል፡፡

ይህንን ለማሳካት የግንዛቤ ማስጨበጫ የውይይት መድረክ ይዘጋጃል፤ በዘርፉ ከተሰማሩ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡ በዚህም መሰረት 2013 እሴት ተጨምሮለት ለገበያ የቀረበ የቡና ምርት ከተደረሰበት 1,400 ቶን ወደ 1,470 ቶን ለማድረስ እና እሴት ተጨምሮለት ለገበያ የቀረበ የቅመማቅመም ምርት በ2013 ከተደረሰበት 7,250 ቶን ወደ 7,612 ቶን ለማድረስ ግብ የተያዘ ሲሆን፡- ግቡን ለማሳካት፡-

- ለአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ቡድን ከተፈቀደው የሰው ኃይል ውስጥ የተወሰነ በማሟላት ሥራው እንዲጠናከር ይደረጋል፤
- የዕሴት ጭመራ ስራን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚረዱ የአስራር ስርዓቶች ይዘጋጃሉ፤
- ሥነ-ምህዳርን መሰረት በማድረግ የተሻሻሉ አሰራሮችና የአግሮፕሮሰሲንግ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ዙሪያ ለዘርፉ ተዋንያንና የባለሙያዎችን የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በኢንዱስትሪዎች የምርት ዝግጅትና ዕሴት ጭመራ ሥራዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በዓይነትና በብዛት ተለይተው እንዲቀርቡ ድጋፍ ይደርጋል፤
- ዕሴት በሚጨመርባቸው ምርቶች የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ከሚመለከታቸው አካላት የመሰብሰብና የማደራጀት ስራ ይሰራል፣
- በዕሴት ጭመራ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን በመስክ በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፣
- በቡናና ቅመማ ቅመም ምርቶች ዕሴት ጭመራ ላይ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች የተጣራ መረጃ ይሰባሰባል፣
- በዕሴት ጭመራ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች ግንኙነትና ውጤታማነት ለማጠናከር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መድረኮች ይዘጋጃሉ፣

### 8.1.8. የልማት አካላት ግንኙነት ማጠናከር

በቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት ሥራ ላይ የተሰማሩትን አርሶ አደሮች፣ የግል አልሚ ባለሃብት፣ የምርምርና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲሁም በየደረጃው ከሚገኙ ማህበራት፣ ዩኒየኖች፣ መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ክልሎች፣ የልማት አጋሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችሉ መድረኮችና ፎረሞችን በማካሄድ ቅንጅታዊ አሰራሮችን ለማሻሻል ጥረት ይደረጋል፡፡

#### የባለ ድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ማዘጋጀት

የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ባለድርሻ አካላትን በማወያየትና ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመለየት፣ ቀጣይ የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥና አፈጻጸማችን በላቀ ደረጃ ለመሳደግ የአማካሪ ካውንስሉ መድረክ በዓመት

አንድ ጊዜ፣ የቡና እሴት ሰንሰለትን ለማጠናከርና ለማዘመን ይረዳ ዘንድ የቡና ፕላትፎርም በዓመት 1 ጊዜ፤ የቅመም ቅመም እሴት ሰንሰለትን ለማጠናከር ፕላትፎርሙን በዓመት 1 ጊዜና የሻይ አውት ግሮወርስ ትሥሥርንም ለማጠናከር በዓመት አንድ ጊዜ፤ በድምሩ 4 ጊዜ በተጨማሪም የኤክስቴንሽን ተደራሽነት የእርካታ ዳሰሳ ጥናት እንዲሁም የቡና እና ቅመማ ቅመም ምርት ዳሰሳ ጥናት ምክክር ለማካሄድ ግብ ተይዟል፡፡

**የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም አውት ግሮወርሰ ትስስር ማጠናከርና ማስፋፋት**

በቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት ሥራ ላይ የተሰማሩ አርሶ አደሮች በክላስተር ወይም በህብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት በአቅራቢያቸው ከሚገኙ አልሚ ባለሃቶች ወይም የልማት ድርጅቶች ጋር ያለውን የትስስር ሂደት ለማጠናከር 20 አልሚ ባለሃብቶችና የልማት ድርጅቶችን በመስክ ለመደገፍና መረጃን ለማጠናከር ታቅዷል፡፡

### 8.1.9. የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር አሠራርን ማዘመንና ማጠናከር

የቡና፣ ሻይና ቅመማቅመም ልማት ዘርፍ ለኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት ያለውን ድርሻ እንዲወጣ ለማስቻል የተጠናከረ የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ግብረ-መልስ አሰራርን መከተል ወሳኝ ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ በየደረጃው ባሉ ፈጻሚ አካላት ወቅታዊ የአፈጻፀም ክትትልና ግምገማ የሚደረግበትን ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ሽፋኑን 100 ፐርሰንት ውጤታማነቱን 87 በመቶ ለማድረስ ግብ ተይዟል፡፡

በዚህ መሰረት በቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት ላይ የክልሎችን የልማት ሥራዎችን በመስክ በመገኘት በየሩብ ዓመቱ ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ በማድረግና ግብረ-መልስ በመስጠት ሽፋኑን 100% ውጤታማነቱን 87% ለማድረስ ግብ ተይዟል፡፡

### 8.1.10. የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም መገንባታ

**የምርጥ ተሞክሮ ሰነዶችን መቀመር**

በ2014 በጀት ዓመት 2 የምርጥ ተሞክሮ ሰነዶች (በቡና፣ በሻይ እና በቅመማ ቅመም ልማት ላይ የተመዘገቡ አዳዲስ መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድና በማረጋገጥ በሥልጠናና በተለያዩ አማራጮች ተመሳሳይ ሥነ-ምህዳር ወደአላቸው አካባቢዎችና ተጠቃሚዎች እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

**የልምድ ልውውጥ ማካሄድ**

ምርጥ ተሞክሮን ማስፋፋት የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ልምድን በማዳበር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም ጥራትን በማሻሻል ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በቡና ሻይና ቅመማ ቅመም አብቃይ ክልሎች በተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎች ላይ ባለሙያዎችና አርሶ አደሮች የልምድ ልውውጥ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም በቡና እና ቅመማ ቅመም ልማት ኤክስቴንሽን ላይ ሁለት ዙር 300 ለሚሆኑ ተሳታፊዎች የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ዕቅድ ተይዟል፡፡

**ስልጠና መስጠት**

የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ በተግባር የተደገፈ ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት 4 ዙር 410 ተሳታፊዎችን ለማሰልጠን ታቅዷል፡፡

ለ1200 ባለ ልዩ ጣዕም ቡና ዉድድር ተሳታፊዎችና ባለሙያዎች የልዩ ቡና አዘገጃጀትና ጥራት አጠባበቅ ስልጠና ከባለድርሻ አካለት ጋር በመተባበር በንድፈ ሃሳብ የሚሰጥ ይሆናል፤ በቅመማቅመም ድህረ-ምርት ዝግጅትና ጥራት አጠባበቅ ላይ ለ120 ለሚሆኑ የክልል፣ ዞንና ወረዳ ባለሙያዎች፤ ከታጠበና ከደረቅ አዘገጃጀት ውጪ ያሉ ዝግጅቶች (anaerobic processing, honey processing, carbonic processing) ላይ በተጋባዥ አሰልጣኞች ለ 40 ተሳታፊዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፣ ለ30 ባለሙያዎች በማአዛማና የመድኃኒትነት ባህሪ ባላቸው ቅመማ ቅመሞች ላይ እና በቡናና ቅመማ ቅመም አሴት ጭመራ ላይ በቁጥር ለ20 ተሳታፊዎች በባለስልጣኑ ባለሙያዎችና በተጋባዥ አሰልጣኝ ስልጠና ለመስጠት ታቅዷል፡፡ ከጠቅላላ ሰልጣኞች ውስጥ 5 በመቶ ወይም በቁጥር 75 ሴት ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ጥረት ይደረጋል፡፡

## 8.2. የወጪ ንግድ መጠንና ገቢ ለማሳደግ የሚከናወኑ ተግባራት

ባለፉት ዓመታት የተከናወኑ ውጤታማ ተግባራትን በማስቀጠል በዚህ ዕቅድ አመትየተጣሉ ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋናዋናተግባራት ተለይተዋል፡፡

### 8.2.1. የምርት አቅርቦትን ማሳደግ

- የቡና አምርች ማህበራትና አነስተኛ አርሶአደሮች በቡና ምርት አለቃቀም እና አያያዝ እንዲሁም የድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ላይ ተግባር ተኮር ስልጠና

በመስጠትና በመደገፍ የእስፔሻሊት ቡና የምርት መጠን አሁን ከደረስንበት 20%ወደ 30% ከፍ ማድረግ፣ የምርት ብክነትን ከ5% ወደ ዜሮ ዝቅ ማድረግ

- አርሶ አደሮች፣ አቅራቢዎችና ላኪዎች በህጋዊ አግባብ በቀጥታ ግብይት ትስስር እንዲገበያዩ በማድረግ የእሴት ሰንሰለት ማሳጠርናየምርት አቅርቦትንመጠን ከ300,133.67 ቶን% ወደ 363,161.74 ቶን ከፍ ማድረግ
- ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 3 ያሉ ቡናዎችን ስፔሻሊትን ጨምሮ አሁን ከደረሰው 50% ወደ 60% ማሳደግ

### 8.2.2. የቀረበውን ምርት ወደ ውጭ ገበያ እንዲላክ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

- 100 ቡና እና 30 የቅመማ ቅመም ላኪ ድረጅቶች በቢዝነስ ፕላን እንዲመሩና ከሀገራዊ ኤክስፖርት ዕቅድ ጋር ዕቅዳቸው እንዲጣጣምበማድረግበወቅቱ ምርት አዘጋጅተው በገቡት ኮንትራት መሰረት ምርታቸውን ወደ ውጭ መላክ እንዲችሉ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- አነስተኛ ቡና አምራች አርሶ አደሮች ያመረቱትን ቡና አዘጋጅተው በቀጥታ ለውጪ ገበያ እንዲያቀርቡ ለ150 አዲስ እና ለ300 ነባር አርሶአደሮች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስ
- በላኪነት ለተሰማሩ ለ800 ነባር እና 50 አዲስ ለሚሰማሩ ድርጅቶች፣ ለ80 ነባር እና ለ5 አዲስ የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች፣ ለ33 በሻይና ቅመማ ቅመም ዘርፍ ለተሰማሩ እና ለ5 አዲስ ለሚሰማሩ የግብይት ተዋንያኖች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስ
- ህብረት ስራ ዩኒዬኖች በወጪ ንግድ ያላቸው የገበያ ድርሻ አሁን ከደረሱበት በመጠን በ10 በመቶ እና በገቢ 15 በመቶ እንዲያድግ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

### 8.2.3. የመረጃ ትንተና በማድረግ የመረጃ አቅርቦት እና የገበያ ድርሻን ማሳደግ፣

- የአለም ዓቀፍ የምርት አቅርቦት፣ የግብይት ዋጋ እና ኤክስፖርት ሁኔታ በሃገር ዓቀፍ ግብይቱ ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ እንዲሁም ሳምንታዊ የቡና ዝቅተኛ ኮንትራት መሸጫ ዋጋ ከአለም ዓቀፍ የቡና ዋጋ እና ከላኪዎች ትርፋማነት አንጻር በቡና አይነትና ደረጃ በመተንተን በየሳምንቱ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ፣

- በነባር የቡና ዋና ዋና የገበያ መዳረሻዎችናበታዳጊ የቡና ገበያ መዳረሻዎች (አውስትራሊያ፣ ሩሲያ፣ ካናዳ እና ቻይና) ላይ ጥናትን መሰረት ያደረገ የገበያ ማስፋፊያ ስራዎችን ማካሄድ፣
- ምርቶቻችን ልዩምልክት (ብራንድ) ያለበት ቋሚ የፕሮሞሽን እቃዎች በመጠቀም ማስተዋወቅና በተጀመረው አግባብ በተለያዩ ሀገራት የብራንድ ምዝገባውን ማካሄድ፣
- አዳዲስ እየተተገበሩ ያሉ የቡና ግብይት ሪፎርሞችን በህጋዊ የግብይት ማዕቀፍ ማካተትና ከዚህ በፊት ይደረጉ የነበሩትን የሬጉላቶሪ የመስክ ቁጥጥር ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል፤
- የሻይ ምርት አቅርቦትና ግብይት ለማሳደግ በአውት ግሮዎርስ ትስስር መመሪያ መሰረት እንዲከናወኑ ከክልሎች ጋር በመቀናጀት መከታተልና መደገፍ፣
- ቡናን በኮንቴነር ወደ ውጭ የመላክ ድርሻን ወደ 100% ከፍ ማድረግና የባቡር ትራንስፖረት አገልግሎት በሚፈለገው አግባብ እንዲቀርብ መደገፍ፤

### 8.2.4. የምርት ጥራት ምርመራ አገልግሎት መስጠት

- በ2014 የኤክስፖርት የጥሬ ቡና ምርት ጥራት ምርመራን በ2013 ከተደረሰበት 330,490 ቶን ወደ 346,910 ቶን ለማድረስ ዕቅድ ተይዟል፡፡ እሴት የተጨመረበት ምርት ምርመራ በመጠን በ2013 ከነበረበት 490 ቶን በ2014 ወደ 910 ቶን ለማሳደግ ይሰራል፤
- በኢትዮጵያ ምርት ገበያና በቡና ግብይቱ ተዋንያን መካከል የሚፈጠሩ የደረጃ ቅሬታዎችን በመቀበል ለቀረቡ ቅሬታዎችበሙሉ ምላሽ መስጠት ፡፡
- የቀረበ ቡና ምርት ከተባይ ቅሪት አካል ነፃ መሆናቸውን የማረጋገጥ ስራን በ2013 ከተደረሰበት 263,550 ወደ 276,727 ቶን በማሳደግ አገልግሎት ይሰጣል
- የምርመራ ውጤትን መሰረት በማድረግ ለቡና ላኪዎች የጥራት ማረጋገጫሠርተፊኬት (Quality Certifícate) እንዲሰጣቸው በማድረግ አፈጻጸሙንከ801 ወደ 828 ማሳደግ፤
- የጥራት ውጤት መግለጫ ሰርተፊኬትም በ2013 ከተደረሰበት 18650 ሰርተፊኬት በ2014 ወደ 19,570 በማሳደግ ትክክለኛና ተአማኒነት ያለው ውጤት ለመስጠት ይሰራል፡፡

- 10,925 የዓለም ቡና ድርጅት የምርት ሀገር ሠርተፊኬት 346,910 ቶን ቡናን ወደ ውጭ ሀገር ለሚልኩት ላኪ ድርጅቶች ይሰጣል
- በበጀት አመቱ ላኪዎች ወደ ውጭ ለሚልኳቸው ቡናዎች ምርመራ በማድረግ ነፃ ሆነው ለተገኙ በቁጥር 7260 የጤና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ለ346,910 ቶን ቡና ) መስጠት፡፡
- በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌሎች በተፈቀዱ የግብይት አማራጮች የተገዛና ርክክብ የተደረገበት 286,839 ቶን የኤክስፖርት አቅርቦት ቡና በአግባቡ በመፈተሽ፣ በፕሎፕ በማሸግ ወደ ኤክስፖርት ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ የሽኝት አገልግሎት መስጠት፣
- ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚዉል 110 ሺህ ቶን የቡና ምርት በመፈተሽ፣ በኘሎኘ በማሸግ ወደ ሸማች አከባቢዎች የመሸኘት አገልግሎት በመስጠት መከታተል፤
- የምርት ክምችት ቆጠራ በዓመት አንድ ጊዜ ማካሄድ፣

### 8.2.5. ቅንጅታዊ አሰራርን ማሳደግ፣

- ስድስት የነበሩትን የቡና ማህበራትን በመሰብሰብ አንድ ጠንካራ ማህበር ማድረግና በጋራ ስራዎችን አብሮ መስራት
- የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት ህገ ወጥ ዝውውር ቁጥጥርከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ማካሄድ፤
- በአቅርቦትና ኤክስፖርት ሂደት የጭነት ተሽከርካሪዎች፣ ባቡር እና የኮንቴነር አቅርቦት እጥረት እንዳይከሰት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ መፍታት
- ለቡና ግዢና ኤክስፖርት የሚውል የብድር አቅርቦት ከባንኮች ጋር ማመቻቸትና አፈፃፀሙን መከታተል
- ለሶስተኛ ጊዜ በሃገራችን የሚደረገውን የባለ ልዩ ጣዕም ቡና ውድድር ከቡና ማህበረሰቡ ጋር በቅንጅት ማከናወን፣
- በወቅታዊ የኤክስፖት አፈጻፀም ዙሪያ ከባለድርሻ አካላትጋር በመቀናጀት በዓመት 4 ጊዜ የምክክር መድረክ ማካሄድና በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ በጋራ መፍታት፣

### 8.2.6. የአሠራር ስርዓቶችን ማሻሻል

- በረቂቅ ደረጃ ያለው የቅመማ ቅመም ጥራት ቁጥጥርና ግብይት ሥርዓት ተጠናቆ እንዲጸድቅ በማድረግ ወደ ተግባር መግባት፣

- አዳዲስ እየተተገበሩ ያሉ የቡና ግብይት ሪፎርሞችን በህጋዊ የግብይት ማዕቀፍ ማካተትና መተግበር፣
- የግብይት ስርዓቱን ለመከታተል የበለፀገውን ሶፍት ዌር ተግባር ላይ ማዋል መከታተልማካተትና መተግበር፣

### 8.3. የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር አሠራርን ማዘመንና ማጠናከር

የቡና፣ ሻይና ቅመማቅመም ልማት ዘርፍ ለኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት ያለውን ድርሻ እንዲወጣ ለማስቻል የተጠናከረ የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ግብረ-መልስ አሰራርን መከተል ወሳኝ ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ በየደረጃው ባሉ ፈጻሚ እና አስፈጻሚ አካላት ወቅታዊ የአፈጻፀም ክትትልና ግምገማ የሚደረግበትን ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ሽፋኑን 100 ፐርሰንት ውጤታማነቱን 87 በመቶ ለማድረስ ግብ ተይዟል፡፡

በዚህ መሰረት በቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት ላይ የክልሎችን የልማት ሥራዎችን በመስክ በመገኘት በየሩብ ዓመቱ ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ በማድረግና ግብረ-መልስ በመስጠት ሽፋኑን 100% ውጤታማነቱን 87% ለማድረስ ግብ ተይዟል፡፡

## 9. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች

**ተግዳሮቶች**

- የቡናና ሻይ ባለስልጣን በኩል የሎጀስቲክ /መኪና/ እጥረት በመኖሩ በክልል ፣ ዞንና ወረዳ ደረጃ ለሚደረግ የድጋፍና ክትትል ሥራዎች ቀደም ሲል በኪራይ መኪናዎች ሲጠቀም የቆየ ቢሆንም በኪራይ መኪና መጠቀም በኦዲት እንደ አሰራር ችግር የተወሰደ በመሆኑ በድጋፍ አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ችግር ተፈጥሯል፡፡ ይህ ችግር በ2014 ከቀጠለ የተቀመጠውን እቅድ ለማሳከት አዳጋች ምሆኑ አይቀረ ነው
- ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሚመደበው ትረዘዠሪ በጀት ከተሰጠው ተልኮ አነፃር በቂ ስለልሆነ በዚህ የበጀት እጥረት ምክንያት የቡና ሻይ እና ቅመማ ቅመም መዋቅራዊ አደረጃጀት እስከ ታች ድረስ ተደራሽ በማድረግ የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

- የቡና ጥራትና ሠርትፊኬሽን ማዕከል የራሱ የሆነ ቋሚ እና ምቹ የአገልግሎት መስጫ ማዕከል የሌለዉ በመሆኑ በተጣበበ ክፍል ውስጥ ለኮሮና በሽታ በሚያጋልጣ ሁኔታ አገልግሎት መስጠት መገደዱ ዋና ዋና ማነቆዎች ናቸዉ፡፡
- በግንቦትና ሰኔ ላይ ከፍተኛ የኮንቴነር እጥረት በማጋጠሙ ብዙ የቡና ኮንትራቶች እንዲራዘሙና ሌሎች ደግሞ እንዲሰረዙ በመደረግ በቡና ኤክስፖርታችን ላይ ከፍተኛ ጫና አደርሷል፡፡

**የመፍትሄ ሃሳቦች**

- መንግስት የባለስልጣን መስሪያቤቱን ችግር በማጠን በቂ በጀት እንዲመደብ ማድረግና ለዘመናት የቆየውን የሎጅስትክ ጥያቄ እንዲመለስ አቅጣጫ ብሰጥበት ባለስልጣን መ/ቤቱ አሁን ከሚሰራው በላይ ውጤታማ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡
- የቡና ጥራትና ሰርትፊኬሽን ማዕከል ችግርም ከዚህ በፍት ለኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት እልባት እንዲሰጥበት ብደረግ ሙሉ በሙሉ ችግሩ መልስ ልያገኝ ይችላል፡፡
- ከኮንተነር አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ሰፊ ውይይት በማድረግ የሚስተዋልባቸው ችግሮች እንዲቀርፉና የተርሚናል አገልግሎት ፍጥነት በሚፈልገው ደረጃ እንዲንቀሳቀስ የተቻላቸውን እንዲያደርጉ ተደርጓል፡፡

## 10. ማጠቃለያ

ባለስልጣኑ ባለፉት አመታት ተልእኮውን ለመወጣት ብርቱ ትግል ሲያደርግ የቆየ ሲሆን በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ውሱንነቶችን በየጊዜው እየገመገመ በማስተካከልና ጠንካራ ጎኖች እንዲጎለብቱ የሚያስችሉ ተግባራትን በመፈጸም ላይ ይገኛል፡፡

በ2014 የምርት ዘመንም የተጀመሩ ሪፎርሞችን አጠናክሮ በማስቀጠል፣ በምርትና ምርታማነት ማሳደጊያ ተግባራትን ከክልሎች ጋር በመቀናጀት አጠናክሮ በማስቀጠል እና ከግብይት ተዋንያንና ባለድርሻ አካላት ጋር የተፈጠሩ የቅንጅት ስራዎች በማጠናከር የዘመኑን የምርታማነት እና የወጪ ንግድ ግቦች ልማሳካት ሁሉ አቀፍ ርብርብ ይደረጋል።

## 11. አባሪ

1. ሰንጠርዥ-1: በ2014 የምርት ዘመን የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርትና ምርታማነት እቅድ

| ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | 2012 የተደረሰበት | የ2013 አፈፃፀም | የ2014 ዕቅድ | የድርጊት መርሀ-ግብር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| ቡና | | | | | | | | |
| በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር ምርት የሚሰጥ የቡና ማሳ ሽፋን | ሄ/ር | 756,852 | 808785 | 818,611 | 818,611 | 818,611 | 818,611 | 818,611 |
| በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር የሚለማ ቡና ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 6.38 | 7.5 | 7.6 | | 7.6 | | |
| በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር የሚገኝ ቡና ምርት | ኩ/ል | 4,825,600 | 6065887.5 | 5,809,288 | | 5,809,288 | | |
| በሰፋፊ እርሻ ኢንቨትመንት ምርት የሚሰጥ ቡና ማሳ ሽፋን | ሄ/ር | 104,583 | 104583 | 113,117 | 113,117 | 113,117 | 113,117 | 113,117 |
| በሰፋፊ እርሻ ኢንቨትመንት ቡና ልማት ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 7 | 7.5 | 8.2 | | 8.2 | | |
| በሰፋፊ እርሻ ኢንቨትመንት የሚገኝ የቡና ምርት | ኩ/ል | 773,914 | 784372.5 | 931,675 | | 931,675 | | |
| ሻይ | | | | | | | | |
| በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር ምርት የሚሰጥ የሻይ ማሳ ሽፋን | ሄ/ር | 463 | 482 | 501 | 501 | 501 | 501 | 501 |
| በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር የሚለማ ሻይ | ኩ/ል/ሄ/ር | 23 | 23 | 24.3 | | | | 24.3 |

| ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | 2012 የተደረሰበት | የ2013 አፈፃፀም | የ2014 ዕቅድ | የድርጊት መርሀ-ግብር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| ምርታማነት | | | | | | | | |
| በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር የሚለማ ሻይ ምርት | ኩ/ል | 10,418 | 1,126 | 12,187 | 3006 | 3006 | 3006 | 3,169 |
| በሰፋፊ እርሻ ኢንቨትመንት ምርት የሚሰጥ ሻይ ማሳ ሽፋን | ሄ/ር | 2,733 | 2,760 | | | | | |
| በሰፋፊ እርሻ ኢንቨትመንት ሻይ ልማት ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 37 | 37 | 38.5 | | | | 38.5 |
| በሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት ሻይ ልማት ምርት | ኩ/ል | 101,121 | 103,040 | 107,321 | | | | |
| ቅመማ ቅመም | | | | | | | | |
| በርበሬ | | | | | | | | |
| መሬት | ሄ/ር | 234,927 | 234,305 | 235,632 | 235,632 | 235,632 | 235,632 | |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 17 | 15.3 | 18.7 | | | 18.7 | |
| ምርት | ኩ/ል | 4,010,000 | 3,588,408 | 4,416,339 | | | 4,416,339 | |
| ዝንጅብል | | | | | | | | |
| መሬት | ሄ/ር | 34,930 | 47,513 | 37,780 | 37,780 | 37,780 | | |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 30 | 28.4 | 29 | | 29 | | |
| ምርት | ኩ/ል | 1,055,000 | 1,350,000 | 1,167,666 | | 1,167,666 | | |
| ጥቁር አዝሙድ | | | | | | | | |
| መሬት | ሄ/ር | 13,101 | 12,530 | 14,999 | 14,999 | 14,999 | | |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 15 | 16.4 | 16.5 | | 16.5 | | |
| ምርት | ኩ/ል | 196,515 | 206,270 | 238,692 | | 238,692 | | |
| ነጭ አዝሙድ | | | | | | | | |
| መሬት | ሄ/ር | 4,957 | 4,579 | 5,675 | 5,675 | 5,675 | | |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 9 | 9.5 | 9.9 | | 9.9 | | |

| ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | 2012 የተደረሰበት | የ2013 አፈፃፀም | የ2014 ዕቅድ | የድርጊት መርሀ-ግብር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| ምርት | ኩ/ል | 46,100 | 43,652 | 55,994 | | 55,994 | | |
| ኮረሪማ | | | | | | | | |
| መሬት | ሄ/ር | 50,000 | 55,000 | 52,020 | 52,020 | 52,020 | 52,020 | |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 7 | 7 | 7.6 | | 7.6 | | |
| ምርት | ኩ/ል | 325,000 | 386,622 | 351,790 | | 351,790 | | |
| አብሽ | | | | | | | | |
| መሬት | ሄ/ር | 26,540 | 24,379 | 27,666 | 27,666 | 27,666 | | |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 11 | 11.7 | 12.1 | | 12.1 | | |
| ምርት | ኩ/ል | 291,940 | 286,217 | 337,122 | | 337,122 | | |
| እርድ | | | | | | | | |
| መሬት | ሄ/ር | 6,616 | 7,277 | 6,816 | 6,816 | 6,816 | 6,816 | |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 37 | 39.7 | 40 | | | 40 | |
| ምርት | ኩ/ል | 244,792 | 288,561 | 273,820 | | | 273,820 | |
| ቁንዶ በርበሬ | | | | | | | | |
| መሬት | ሄ/ር | 745 | 850 | 806 | 806 | 806 | 806 | 806 |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 11 | 11.2 | 12 | | 12 | | |
| ምርት | ኩ/ል | 8,195 | 9,540 | 9,772 | | 9,772 | | |
| ሚጥሚጣ | | | | | | | | |
| መሬት | ሄ/ር | 3,935 | 4,303 | 3,957 | 3,957 | 3,957 | | |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 10 | 9.4 | 10.6 | | 10.6 | | |
| ምርት | ኩ/ል | 39,350 | 40,732 | 41,976 | | 41,976 | | |
| ድንብላል | | | | | | | | |
| መሬት | ሄ/ር | 3,085 | 3,059 | 3,337 | 3,337 | 3,337 | | |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 15 | 15.8 | 16 | | 16 | | |
| ምርት | ኩ/ል | 47,201 | 48,379 | 52,699 | | 52,699 | | |
| ጥምዝ | | | | | | | | |
| መሬት | ሄ/ር | 5,405 | 3,855 | 5,656 | 5,656 | 5,656 | 5,656 | 5,656 |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 4 | 5 | 5.1 | | | 4 | |
| ምርት | ኩ/ል | 21,620 | 19,417 | 24,945 | | | 24,945 | |
| ሮዝመሪ | | | | | | | | |

| ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | 2012 የተደረሰበት | የ2013 አፈፃፀም | የ2014 ዕቅድ | የድርጊት መርሀ-ግብር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| መሬት | ሂ/ር | 400 | | 433 | 433 | 433 | 433 | 433 |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሂ/ር | 10 | 10 | 15.6 | | | | 15.6 |
| ምርት | ኩ/ል | 4000 | | 4769.9 | 1297.9 | 865.3 | 1297.9 | 1308.7 |
| ሌሎች ቅመማ ቅመም((በሶብላ፣ ኮሰረት፣ ጤናዳም) | | | | | | | | |
| መሬት | ሂ/ር | 3507 | 6254 | 3542.2 | | 3542.2 | | |
| ምርታማነት | ኩ/ል/ሂ/ር | 16.5 | | 17.0 | | 17.0 | | |
| ምርት | ኩ/ል | 57700 | 175737 | 60212.1 | | 60212.1 | | |
| የቡና ኤክስፖርት | | | | | | | | |
| የምርት መጠን | መጠን በሺ. ቶን | 270,000 | 240 | 280 | 72 | 54 | 59 | 95 |
| የገቢ መጠን | በሚሊዬን ዶላር | 865.5 | 875.18 | 1.014 | 239.85 | 164.95 | 218.01 | 377.20 |
| የሻይ ኤክስፖርት | | | | | | | | |
| የምርት መጠን | መጠን በሺ. ቶን | 1,533.68 | 1,671.33 | 1.922 | 0.67 | 0.71 | 0.44 | 0.11 |
| የገቢ መጠን | በሚሊዬን ዶላር | 2.36 | 2.650 | 3.07 | 1.12 | 1.03 | 0.70 | 0.23 |
| የቅመማ ቅመም ኤክስፖርት | | | | | | | | |
| የምርት መጠን | መጠን በሺ. ቶን | 10,960 | 12,753.43 | 14.028 | 3,152.63 | 3,167.95 | 3,004.66 | 4,703.54 |
| የገቢ መጠን | በሚሊዬን ዶላር | 15.06 | 15.67 | 17.24 | 3.57 | 3.83 | 3.84 | 6.00 |
| ጠቅላላ ኤክስፖርት | | | | | | | | |
| የምርት መጠን | መጠን በሺ. ቶን | 282,500 | 254,756.60 | 295.95 | 74,700.37 | 56,633.14 | 61,216.57 | 99,581.14 |
| የገቢ መጠን | በሚሊዬን ዶላር | 882.92 | 893.5 | 1,035 | 244.541 | 169.795 | 222.555 | 383.42 |

## ሰንጠረዥ-2: በ2014 በጀት ዓመት የቡና ኤክስፖርት የመጠንና ገቢ ዕቅድ

| ተ.ቁ | የምርት አይነት | የ2013 ክንዉን | | የ2014 ዕቅድ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መጠን በቶን | ገቢ በሚልዬን ዶላር | መጠን በቶን | ገቢ በሚልዬን ዶላር |
| 1 | ሃምሌ | 19,015.91 | 63.97 | 21,339.80 | 71.78 |
| 2 | ነሃሴ | 19,995.48 | 72.69 | 28,455.70 | 97.75 |
| 3 | መስከረም | 14,431.66 | 48.13 | 21,085.40 | 70.31 |
| | | **53,443.05** | **184.79** | **70,880.90** | 239.84 |
| 4 | ጥቅምት | 13,812.86 | 45.74 | 21,226.50 | 70.28 |
| 5 | ህዳር | 14,311.18 | 43.74 | 15,928.30 | 48.69 |
| 6 | ታህሳስ | 10,245.71 | 30.19 | 15,602.80 | 45.98 |
| | | **38,369.75** | **119.67** | **52,757.60** | 164.95 |
| 7 | ጥር | 11,995.13 | 41.63 | 13,409.80 | 46.54 |
| 8 | የካቲት | 15,690.90 | 59.52 | 19,954.50 | 75.7 |
| 9 | መጋቢት | 27,247.23 | 106.85 | 26,907.50 | 105.5 |
| | | **54,933.26** | **208** | **60,271.80** | 227.74 |
| 10 | ሚያዚያ | 28,817.60 | 113.63 | 28,193.30 | 111.2 |
| 11 | ግንቦት | 32,668.18 | 130.52 | 33,527.60 | 133.9 |
| 12 | ሰኔ | 40,079.82 | 150.43 | 34,369.20 | 137.3 |
| | | **101,565.60** | **394.58** | **96,090.10** | 382.4 |
| **ድምር** | | **248,311.66** | **907.04** | **280,000.04** | **1,014.93** |

## ሰንጠረዥ-3: በ2014 በጀት ዓመት የቅመማ ቅመም ኤክስፖርት የመጠንና ገቢ ዕቅድ

| ተ.ቁ | ወራት | የ2013 ክንዉን | | የ2014 ዕቅድ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መጠን በቶን | ገቢ በሚልዬን ዶላር | መጠን በቶን | ገቢ በሚልዬን ዶላር |
| 1 | ሐምሌ | 823.89 | 1.07 | 906.27 | 1.17 |
| 2 | ነሐሴ | 1,108.66 | 1.21 | 1219.53 | 1.33 |
| 3 | መስከርም | 933.48 | 0.96 | 1026.83 | 1.06 |
| | | **2,866.03** | **3.24** | **3152.63** | 3.56 |
| 4 | ጥቅምት | 920.23 | 1.13 | 1012.26 | 1.25 |
| 5 | ሕዳር | 997.63 | 1.06 | 1097.4 | 1.16 |
| 6 | ታህሳስ | 962.09 | 1.29 | 1058.3 | 1.42 |
| | | **2,879.96** | **3.48** | **3167.96** | 3.83 |
| 7 | ጥር | 500.75 | 0.76 | 550.83 | 0.83 |
| 8 | የካቲት | 629.57 | 1.06 | 692.52 | 1.17 |
| 9 | መጋቢት | 1,601.18 | 1.68 | 1761.3 | 1.85 |
| | | **2,731.51** | **3.5** | **3004.65** | 3.85 |
| 10 | ሚያዚያ | 1,737.53 | 1.69 | 1911.28 | 1.86 |
| 11 | ግንቦት | 1,269.21 | 1.88 | 1396.1 | 2.07 |
| 12 | ሰኔ | 1,269.21 | 1.88 | 1396.13 | 2.07 |
| | | **4,275.95** | **5.45** | **4703.51** | **6.00** |
| **ድምር** | | **12,753.43** | **15.67** | **14,028.75** | **17.24** |

ሰንጠርዥ-4: በ2014 በጀት ዓመት የሻይ ኤክስፖርት የመጠንና ገቢ ዕቅድ

| ተ.ቁ | ወራት | የ2013 ክንዉን | | የ2014 ዕቅድ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መጠን በቶን | ገቢ በሚልዬን ዶላር | መጠን በቶን | ገቢ በሚልዬን ዶላር |
| 1 | ሐምሌ | 209.576 | 0.371 | 241.01 | 0.43 |
| 2 | ነሐሴ | 125.685 | 0.257 | 144.54 | 0.3 |
| 3 | መስከርም | 244.595 | 0.347 | 281.28 | 0.4 |
| | | **579.856** | **0.975** | **666.83** | 1.13 |
| 4 | ጥቅምት | 178.519 | 0.18 | 205.30 | 0.21 |
| 5 | ሕዳር | 143.921 | 0.235 | 165.51 | 0.27 |
| 6 | ታህሳስ | 292.855 | 0.468 | 336.78 | 0.54 |
| | | **615.295** | **0.883** | **707.59** | 1.02 |
| 7 | ጥር | 112.563 | 0.2 | 129.45 | 0.23 |
| 8 | የካቲት | 163.604 | 0.277 | 188.14 | 0.32 |
| 9 | መጋቢት | 106.536 | 0.127 | 122.52 | 0.15 |
| | | **382.703** | **0.604** | **440.11** | 0.7 |
| 10 | ሚያዚያ | 44.638 | 0.084 | 51.33 | 0.1 |
| 11 | ግንቦት | 24.418 | 0.052 | 28.08 | 0.06 |
| 12 | ሰኔ | 24.418 | 0.052 | 28.08 | 0.06 |
| | | **93.474** | **0.188** | **107.49** | **0.22** |
| **ድምር** | | **1,671.33** | **2.65** | **1,922.02** | **2.85** |